
# የነፃነት ጎህ ሲቀድ


ጠሀፊ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ
ቅኝት መስፍን ማሞ ተሰማ


## የቅኝት ትኩረት - በአሰብ ጥያቄ ዙሪያ

<u>*መንደርደሪያ*</u>




የነፃነት ጎህ ሲቀድ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን ህዝባችን ለዴሞክራሲያዊና መልካም አስተዳደር መቆም ያደረገውን ልዩና ታላቅ የተጋድሎ ታሪክ በታሪክ መዘክርነት ያቀረበ ታሪካዊ መጥሀፍ ነው።

ይህንን መጥሀፍ ብርቅዬ የሚያደርገውም ኢህአዴግ የህዝብን ለዴሞክራሲያዊ መብት ትግል በጠመንጃ አፈሙዝ አኮላሽቶ የህዝባችንን አመኔታ (ትረስት) እና ይሁንታ (አክሴፕተንስ) ያገኙትን የህዝብ ተመራጮች በግፍና ኢፍትሃዊ መንገድ እስር ቤት ካስገባቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ወኪሎች መኻል አንዱ የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ጥፈው ለአደባባይና ለትውልድ ማብቃታቸው ይሆናል።

እርግጥ ነው ትውልድ ያልፋል፤ ትውልድ ይተካል። ሀገርና ታሪክ ግና አያልፉም። የነፃነት ጎህ ሲቀድ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የታሪካችን ሠነድ አንድ አካል ሆኗል።

በዶክተር ብርሃኑ አልበገርባይነት፤ የህሊናን ልጓም ገትቶ ራስን አረጋግቶና ከራስ ጋር ታርቆ የነፃነት ጎህ ሲቀድ የሚያህልን የታሪክ ቅርስ በፍፁም ግልፅነት ጥፎ ማቅረብ እንደምን ያለ አዳጋች ጭርሱንም የማይታሰብ እንደሆነ - በኢትዮጵያ እስር ቤቶች የፖለቲካ እስረኛ ሆኖ አመታትን ያስቆጠረ ሁሉ ከማንም በላይ ጠንቅቆ ይረዳዋል።

የነፃነት ጎህ ሲቀድ በአራት አበይት ክፍሎች ተዋቅሮ በርካታ ንዑስ ጉዳዮችን በ614 ገጦች ያካተተተ ሆኖ ይገኛል። የታሪኩ አብላጫ ክፍል በቅንጅት ምሥረታ፤ የምርጫ 1997 ዓ/ም ተሳትፎና ትግል፤ እና በምርጫው ማግስት የተከሰተውን የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ድባብ በዝርዝር ይዳስሳል። የህትመት ዘመኑ እአአ በ2006 ሆኖ የህትመት ስፍራውም በሰሜን አሜሪካ ነው።

የዚህ ቅኝት አቅራቢ ትኩረት ግና በቅንጅትና ከቅንጅት ትግል ጋር በተያያዘ የነፃነት ጎህ ሲቀድ ባቀረበው ታሪክ ዙሪያ ከቶም አይደለም።

ሕዝባችን ለዴሞክራሲያዊ መብቱ ባመነበት አደረጃጀትና የፖለቲካ ቅያስ ከቅንጅት ጎን በመቆም ያደረገው የመስዋዕትነት ትግል መቼም ይሁን መቼ መከበርና መዘከር አለበት የሚል ፅኑ ዕምነት አለኝ።

የዚህ ቅኝት መነሻና መድረሻ በመጥሀፉ ውስጥ በተወሰኑ ሀገራዊ አበይት ነቁጦች ላይ ጠሀፊው ባንጠባረቁት *ፖለቲካዊ ዕምነት ወይም መርህ ዙሪያ ብቻ ያተኮረ ነው* እንጂ ከቶም በምንም አይነት መልኩ ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ጠሀፊ ዛሬ ከሚያራምዱት ፖለቲካዊ አመለካከታቸውም ሆነ መንገዳቸው ጋር አንዳችም የሚያዛምደው ሰበዝ አለመኖሩን አንባቢያን ልብ ይሉት  ዘንዳ አስፈላጊ ይሆናል። ቅኝቱ ከጀርባውም ሆነ ከጎኑ ያዘለው ወይም ያንጠለጠለው አንዳችም ተልዕኮ ወይም ድብቅ ዓላማ የሌለው ሲሆን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነቴ በኢትዮጵያ ላይ የቀረቡትን ዘገባዎች አንብቤ የተሰማኝን ነፃ (ከየትኛውም ድርጅት ቡራኬም ሆነ ቁርኝት የፀዳ) ዴሞክራሲያዊ አስተያየት የመስጠት ዜግነታዊ መብቴን በመጠቀም እንጂ።

ከጎጠኝነት በፊት ኢትዮጵያዊነታቸውን አስቀድመው ለተደራጁና ለነገይቷ ኢትዮጵያ ሠላም ብልፅግናና እድገት የሚሆናትን መልካም የህዝብ አስተዳደር ለማቆም ለሚታገሉ ተቃዋሚ ህብረ ብሄር ድርጅቶች ሁሉ በመርህ ደረጃ የማያወላውል አክብሮትና ድጋፍ ያለኝ ሲሆን ህብረ ብሄራቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት የሚጓዙባቸው መጋቢ መንገዶችም ወደ አንድ አውራጎዳና (ምንም እንኳን ዘመኑ ቢጓተትም) ያመራሉ የሚል ተስፋና ዕምነት አለኝ።

የነፃነት ጎህ ሲቀድ ላይ ያቀረብኩት ቅኝት አደረጃጀት በተነሱት ነጥቦች ላይ ብቻ ያቀነቀነ እንጂ ሰብእናን የሚጋፋ ወይም የትላንቱን (የመጥሀፉን ይዘት) ከዛሬ ሁኔታ ጋር ጎትቶ ያዳበለ ላለመሆኑ ታዳሚያን ያስተውሉት ዘንዳ አስፈላጊ ይሆናል። እናዝግም ወደነጥቡ፤

***መጥሀፍን በሽፋኑ አትመዝነው***

ከላይ የተጠቀሰው አባባል የመጣህፍት አንባቢያን ያልተደነገገ ዐለም ዓቀፋዊ ግንዛቤ ነው። አንድ መጥሀፍ ሽፋኑ ስለማይስብ ይዘቱም አይረባም ወይም ሽፋኑ ስላማረ ይዘቱም አርኪ ይሆናል ብሎ መፍረድ አይቻልምና።

የነፃነት ጎህ ሲቀድ በሽፋኑ ላይ ይዞት የቀረበው ምስል ግና መጥሀፉ ሊነግረን ከሚችለው በላይ በጠራ ቋንቋ ብዙ ነገር ያስጨብጠናል። የመጀመሪያውን ምዕራፍ ገጥ ከመግለጣችን አስቀድሞ ስለመጣህፉ ይዘት ወደ አንዳች ግምጋሚ እንድናመራ ወይም በአእምሯችን የጥያቄ ድርድር እንዲጉላላ ያስገድደናልና!

መጥሀፍን በሽፋኑ አትመዝን የሚለውን ሁለንተናዊ መግባቢያ የነፃነት ጎህ ሲቀድ አሽቀንጥሮ የጣለ በመሆኑ ሳናነበው ልንዳኘው፤ ሳንመረምረው ልንፈርጀው የተገደድን ስንቶቻችን እንሆን?

በህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ /ህወሃት/ እና በኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር /ሻዕቢያ/ መካከል አዲስ አበባ ላይ የተለወጠውን የኢትዮጵያን ካርታ የነፃነት ጎህ ሲቀድ ስለምን መለያው አደረገው? ከዚህ ይልቅ ድፍን የጦቢያን ህዝብ የሚወክለውን ባንዲራችንን መጠቀሙ አይሻልም ነበርን? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ገና የመጥሀፉ መጀመሪያ ገጥ ሳይነበብ በህሊናችን ውስጥ መሰለፍ ከሚጀምሩት ጥቂቶቹ ናቸው። እናም ለኒህና ምናልባት ለሌሎችም ጥያቄዎች መልስ እናገኝ ዘንዳ ወደ መጥሀፉ መዝለቅ ግድ ይለናል።

## *የነገሩንን ፈጥመዋል፤ የፈጠሙትንም ያምኑበታል*

ህወሃትና ሻዕቢያ አዲስ አበባን ከመቆጣጠራቸው በፊት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት ወታደራዊ የበላይነትን ባገኙበት የ1982 ዓ/ም መጨረሻዎቹ ወራት አቶ መለስ ዜናዊ ከጫካ በሚተላለፈው የሬዲዮ ስርጭታቸው ሠፊ መግለጫ ሰጥተውን ነበር።

ከጊዜው መርዘም አኳያ የዚህ ቅኝት አቅራቢ የአቶ መለስን ዲስኩር ቃል በቃል ማስታወስ ባይችልም በጥቅሉ ከተናገሩት/ከነገሩን ውስጥ *“ድርጅታችን አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ የፖለቲካ መርሃ ግብራችንን ተግባራዊ ማድረግ እንጀምራለን። የመጀመሪያው ተልዕኳችንም የኤርትራን ነፃነት ማረጋገጥ ይሆናል”* የሚል ይዘት ይገኝበታል።

ምንም እንኳን በደርግ ዘመነ መንግሥት የፖለቲካው ሰለባዎች ከሆኑት መካከል ይህ ጠሀፊ አንዱ ቢሆንምና ደርግ መለወጥ እንደነበረበት ቢያምንም ከላይ ከተጠቀሰው የአቶ መለስ ኦፊሴላዊ መግለጫ በኋላ ህወሃት/አህአዴግ ከቶም ለኢትዮጵያ ሊበጃት የማይችል የፖለቲካ አማራጭ ሀይል ነው የሚል ፅኑ አቋም በመያዝ የህወሃት/ሻዕቢያን ወደ አዲስ አበባ ግስጋሴ በማንኛውም መንገድ - ከወቅቱ የመከላከያ ሰራዊታችን ጎን በወታደራዊ ትንቅንቁ መሳተፍን ጨምሮ - መግታት ያስፈልጋል ብለው ከተሰለፉት ጎራ ወግኖ ነበር። ነበር ብቻም ሳይሆን ከአስር ሺህ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ጋር ለወታደራዊ ትንቅንቁ ሥልጠናም ወደ ብላቴ /አየር ወለድ ማሰልጠኛ ከምፕ/ ዘልቆ ለሁለት ወራት ቆይቷል። (በዘመኑ ህወሃት በብላቴ የከተተውን የተማረ ሃይል ‘እንግሊዝኛ ተናጋሪው ጦር’ የሚል የምፀት ስም አውጥቶለት ነበር።)

አቶ መለስ ዜናዊ ጫካ ሆነው የነገሩንን በለስ ቀንቷቸውና አሜሪካኖች አመቻችተውላቸው ከተማ ሲገቡ ቃላቸውን አላጠፉም። እነሆ ከግንቦት 1983 ዓ/ም ዠምሮ አየህ ዘመን ድረስ በዘለቀው ገዢነታቸውም ከበረሃ ያስተላለፉልንን የድርጅታቸውን መርሃ ግብር/ፕሮግራም ሳያዛንፉና ሳይሰንፉ ዕውን ከማድረግ አንዲትም ጋት አፈግፍገው አያውቁም። ምናልባት ያኔ የረሱትን ወይም አደባባይ ያልነገሩንን የሀገራችንን ለም ግዛቶች በሙሉ ለባእዳን ባለሀብቶች ለዘመናት በቅኝነት መቸብቸባቸው ካልሆነ በቀር። እናም **ከመነሻቸው የሚያደርጉትን ነግረውናል። የነገሩንን ፈጥመዋል። የፈጠሙትንም ያምኑበታል።**

ከዚህ አንጣር ህወሃት አስገራሚ ድርጅት ሆኖ ይገኛል። አስገራሚነቱም በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘረኛ አገዛዙ ወይም መንግሥትነቱ የፈጠማቸውንና የሚፈጥማቸውን በግልጥ ተናግሮ የተገበራቸውና የሚተገብራቸው ብቻ ሳይሆን ሽንጡን ገትሮ ስለትክክለኛነታቸው የሚሟገት መሆኑም ጭምር ነው።

በአንጣሩ ደግሞ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉት የሀገራችን ፖለቲከኛ ምሁራን ፖለቲካዊ አመለካከት፣ አቋምና ራዕይ ያስደነግጣል፣ ግራ ያጋባል፣ ያሳስባል። በዚህ ቅኝት አቅራቢ ላይ ሶስቱንም አይነት ስሜቶች ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ መጥሀፍ ፈጥሮበታል። እንዴት? ማለት መልካም ነው፣ እነሆ ምላሹን በሚከተለው ይጀምሯል።

*“ኢህአዴግ አብዛኛው ህብረተሰብ ወደሚፈልገው ዐይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት አገሪቱን ሊወስዳት ይችላል። በፍጥነት እንኳን ባይሆን በዝግታ ግን በእርግጠኝነት ወደዚያ ይሄዳል የሚለውን አዎንታዊ ስሜት እኔም እጋራው የነበረ ነው። ይህንንም ስለማምን ነበር በተሰማራሁበት መስክም ሆነ እንዲሁ እንደ ዜጋ በይፋ (በኦፊሴል) በምፅፋቸው ፅሁፎችም ሆነ በግል የኢህአዴግን ባለሥልጣናት በማገኝበት ጊዜ በእኔ ግምት ስህተት ናቸው ብዬ*

*የማምናቸውን እርምጃዎቻቸውን ያለምንም ይሉኝታ በግልፅ እነግራቸው የነበረው።"* (ገጥ125 አፅንዖት የቃኚው)

ይህ አመለካከት ምናልባት ከቀናነት የመነጨ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ይሁንና ኢህአዴግ ከግንቦት 1983 ዓ/ም ዠምሮ ሀገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት እየመራት ሳይሆን የነበረው በእርግጠኝነት ግን በረሃ የነደፈውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህወሃታዊ መርሃ ግብሩን እየተገበረ ነበር የነበረው።

አስቀድሞ ለአብነት ያቀረብኩት 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ በኢህአዴግ ላይ የነበራቸው አመለካከት ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን በመጣ እጅግ ቢበዛ ሶስትና አራት አመታት ውስጥ የነበራቸው አቋምና አመለካከት ቢሆን አይደንቀንም። ግና ይህ በህወሃት ላይ የነበራቸው አቋም እስከ 1997 ዓ/ም (ለአስራ አራት ዓመታት) የዘለቀ እና የነፃነት ጎህ ሲቀድን በሚጥፉበት ወቅትም (ወደፊት እንደምንቃኘው) ጭምር የነበረ ሆኖ ይገኛል።

ኢህአዴግ እንዳይደነብር 'ሂሳዊ ድጋፍ' በመስጠት በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል የሚለው አቋማቸው ወይም ፖለቲካዊ እምነታቸው አስራ አራት ዓመታት (እስከ 1997 ዓ/ም) መዝለቁ እህአዴግ በሀገራችን ላይ ከፈጠማቸው የአስራ አራት አመታት ጥፋቶች በምንም አይነት መልኩ ፖለቲካዊ ሚዛን ሊደፋ የሚችል አቋም ነበር ለማለት ያስቸግራል፣ አልነበረምም። ደግሞስ ቢሆን ኢህአዴግ ደነበረ አልደነበረ - በኢትዮጵያ ላይ ከፈጠመው ሀገራዊ ክህደት፣ ህገወጥና ዘረኛ ድርጊት በላይ ምን ሊፈጥም ይችል ነበር?

ከዚህ በተጨማሪ አስደማሚ የሚሆነው ደግሞ እንደነ አቶ በረከት ስምዖን ያሉትን ወይራ የኢህአዴግ አመራሮች ጭምር 'ስህተታቸውን እየጠቆሙ' እና 'ሂሳዊ ድጋፍ' እየሰጡ ለሚቀጥለው የታረመ እርምጃ እንዲወስዱ ያለማመንታት እነግራቸው ነበር ያሉት ነው።

እንደ ህወሃት ያለ ባለ ሁለት ስለት ካራ ያላቸው ምላጭ የፖለቲካ አመራሮች ያሉትን ድርጅት በ'ሂሳዊ ድጋፍ' መቀየር ወይም ከመጪ 'ስህተት' እንዲታቀብ ማስተካከል ይቻላል በሚለው ፖለቲካዊ አመለካከት ተጠቃሚው ማን ነበር? ህወሃት የሀገር ሉዐላዊነትን ከመናድ፣ ዘረኝነትን ከማስፈን፣ ኢትዮጵያዊነትን ከመገዝገዝ ወዘተርፈ ተግባራቱ ለመሆኑ ሥልጣን ከጨበጠበት ሰአትና ቀን አንስቶ ላፍታ እንኳ ታቅቦ ያውቃልና ነበር 'ስህተታቸውን እንዳይደግሙ' 'ሂሳዊ ድጋፍ' ያስፈለጋቸው? ከዚያ በላይ ምን ሊፈጥሙስ ይችሉ ነበር? የሚከተለውን ነቁጥ ያስተውሏል፣

*"ኢህአዴግን በሚመለከት ሁልጊዜም ከራሴ ጋር የሚያሟግተኝ ይህ ድርጅት መንግሥት ከሆነ በኋላና መንግሥት በመሆን ከሚመጣው ሃላፊነት አንፃር ስህተቶቹ ሲነገሩት መስማትና ማሻሻል የሚችል ድርጅት ነው ወይስ እንዴ የሚያምንበትን እምነት ምንም ይሁን ምን የሚገፋበት ግትር ድርጅት ነው? የሚለው ጥያቄ ነበር።""* ገጥ 20 (አፅንዖት የኔ)

በበኩሌ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ህወሃት/እህአዴግ/ሻዕቢያ በ1983 ዓ/ም ኮንፍረንስ ላይ በማያሻማና በጠራ ቋንቋ ምላሽ ሰጥቷል። ማመን ያልፈለግነው ወይም ከእባብ እንቁላል ርግብ መጠበቅ የጀመርነው እኛ ለሀገርና ለህዝብ ዘላቂ 'ራዕይ' አለን የምንለው ነበርን፣ በተለይ ግን ምሁራኑ። በዚህ መሰረታዊ ስህተታችን መዘዝ ዛሬ ድረስ እየከፈልንበት የምንገኝ መሆናችን ብቻ ሳይሆን የየበኩላችን ቀጥተኛም ይሁን ልዝብ (ፓሲቭ) አስተዋፅዖ እንደነበርም ማመን መቻል ይኖርብናል።

እነሆ የነፃነት ጎህ ሲቀድ ጠሀፊ አስቀድሞ ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከአስራ አራት ዓመት በላይ (እስከ 1997ዓ/ም) ወስዶባቸዋል። ይህ እንደምን ሊሆን ቻለ? ለሚለው

ግን መጥሀፉን አንብበንም ስንጨርስ ምላሹን ለማግኘት እንቆቅልሽ እንደሆነብን ነው የሚቀረው።

## ኢትዮጵያ የባህር በር (ወደብ) አያስፈልጋትም

*"ለብዙ ኢትዮጵያውያን ብሄረተኞች ኤርትራ የተገነጠለችበት ሁኔታ ጥሩ ስሜት ያልፈጠረ ቢሆንም በጊዜው ሊያቆሙት የማይችሉት እና በጉልበት በኤርትራ ጦርነት የተፈፀመ በመሆኑ...**የኤርትራን መገንጠል እያንገራገሩም ቢሆን ለመቀበል ፈቃደኞች ነበሩ።**"* ገጥ 122 (አፅንዖት የኔ)

ለመሆኑ 'የኤርትራን መገንጠል እያንገራገሩም ቢሆን የተቀበሉት የኢትዮጵያ ብሄረተኞች' እነማን ናቸው? ብለን መጠየቅ እንገደዳለን። የኢትዮጵያ ህዝብ በኤርትራ መገንጠል ላይም ሆነ የተገነጠለችው ኤርትራ መያዝ በነበረባት የድንበር መስመር ዙሪያ ከቶም ድምፁ በህወሃት ሻዕቢያ ታፍኖ በሁለቱ ፀረ ኢትዮጵያ ሃይላት ውሳኔ ብቻ የፀደቀ ለመሆኑ የሚያጠያይቀን አይሆንም። ይህንንም ፀረ ኢትዮጵያ ውሳኔ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ያወገዙትና የተቃወሙት ነበር፤ ነውም። በመሆኑም "...እያንገራገሩም ቢሆን የተቀበሉት የኢትዮጵያ ብሄረተኞች'" የተባሉት የትኞቹ የህዝባችን ክፍል አባላት እንደሆኑ ከቶም ግልጥነት የለውም። ደግሞም የወቅቱን ነባራዊ እውነታ የሚገልጥም ሆኖ አይገኝም። በመሆኑም ከኤርትራ መገንጠል ጋር በተያያዘ ያለውን ታሪክ በአግባቡ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ባለማስቀመጡ 'ለምን?' ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን።

*'አሰብ የማን ናት?'* በሚለው ዶ/ር ያዕቆብ ሃ/ማርያም ባበረከቱልን እጅግ ጠቃሚ የታሪክና የህግ ሰነዶችን ያካተተው መጥሀፋቸው ውስጥ የሚከተለውን የጥሁፍ መረጃ እናገኛለን፤

*"በግንቦት 1983 ዓ/ም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሻቢያ አሥመራን ከተቆጣጠሩ በኋላ ኢህአዴግ የሠላም ጉባኤ ያለውን ስብሰባ ጠርቶ በአብዛኛው የብሄር ብሄረሰቦች፤ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች በጉባኤው ተገኝተው ካስተላለፉዋቸው ውሳኔዎች አንዱ የኤርትራን ነፃነት ማፅደቅ ማለት ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበር።...*

*"...ጉባኤው አንዳንድ ብሄረሰቦች እንወክላለን ያሉ ግለሰቦች የሲቪል ማህበራትና የጥቂት ፓርቲዎች መሪዎች ነን ባዮችና በጦርነቱ ደርግን አሸንፈው ሥልጣን የጨበጡ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙበት ሲሆን **ማናቸውም በህዝብ የተመረጡ ህዝብን የሚወክሉ አልነበሩም።** ይህም በመሆኑ **ጉባኤው ምናልባት የአገሪቱን ሠላም ለማስጠበቅ የሽግግር መንግሥት ከማቋቋሙ ውጪ ሌላ በሀገሪቱ ላይ አሳሪ የሆነ ግዴታ ውስጥ የሚከት በተለይም የአገሪቱን አንዱን ክፍል የሚገነጥል ውሳኔ ለመወሰን ሥልጣን አልነበረውም።** ጉባኤው ግን በሌለው ሥልጣን እንዲያውም የኢትዮጵያ ህግ በመተላለፍ በህዝብ ያልተመረጠ ስብስብ ቀርቶ ህዝብን የሚወክል ፓርላማ እንኳን ሊያደርገው ሥልጣን በሌለው በአገር አንድነት ጉዳይ ውሳኔ ሰጠ። በአፄ ሃይለሥላሴ ከተደነገገው ከ1923 ዓ/ም ህገ መንግሥት አንስቶ እስከ ደርግ ህገ መንግሥት አንዳቸውም አንዲት ጋት የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ አሳልፎ መስጠት ወይም ማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ማስገንጠል አይፈቅዱም ነበር። ምናልባት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ መንግሥት ወይም አገር ሊሰጥ የሚችለው መላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ በህዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) ሲስማማ ብቻ ነው።"* በማለት ዶ/ር ያዕቆብ በወቅቱ ኤርትራ ስለተገነጠለችበት ህገወጥ መንገድ በስፋት ጥፈዋል። (አፅንዖት የቃኘው)

‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ግን እንኳንና እንዲህ ያለውን የወቅቱን አይን ያወጣ የኤርትራን አገነጣጠል ታሪክ በታሪክነት በአግባቡ ዘግቦ ለትውልድ ያቆየ ወይም ያስተላለፈ ሊሆን ቀርቶ ጭርሱንም “የኢትዮጵያ ብሄረተኞች እያንገራገሩም ቢሆን ለመቀበል ፈቃደኞች ነበሩ” ሲል የማናውቀውን መርዶ ያረዳናል። የዛሬው ብቻ ሳይሆን የነገው ትውልድ ይህንን ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ የታሪክ ዘገባ ሲያነብ ምን ሊረዳ ይችላል? የሚለው ጥያቄ የታሪክ ዘጋቢዎችን በብረቱ ሊያሰሳስብ የሚገባ መሰረታዊ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል። በዚህ አንጣር ላለውም ሆነ ለመጪው ትውልድ ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ የታሪክን ዕውነታ በአግባቡ አላቀረበም።

በግንጠላው ጉባኤ ላይ ከነበሩት መካከል ለምሳሌ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ተቃውሟቸውን አሰምተው ነበር። ፕሮፌሰር አሥራት ሲናገሩ፤ *“አሰብ በታሪክም በህግም የኢትዮጵያ የባህር በር ስለሆነች ወደ ኢትዮጵያ መካለል አለባት”* ባሉ ጊዜ አቶ ኢሳያስ *“ታሪክና ህግ የሚሉት ዝባዝንኬ ለትምህርት ቤት ክፍል ይተዉት። ይህ ፖለቲካዊ ጉዳይ በጦር ሜዳ ተፈቷል” በማለት ተሳለቁባቸው፤* ሲል በኮንፍረንሱ ላይ የነበረውን የታሪክ እውነታ *“አሰብ የማን ናት?”* የሚለው የዶ/ር ያዕቆብ መጥሀፍ በታሪክነት ዘግቦታል። *“የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አቋም (ኤርትራ አሰብን ጨምራ መገንጠሏን መቃወማቸው) በፖለቲካውም ሆነ በህጉ አንፃር ሲታይ በፅኑ መሰረት ላይ የቆመ ነበር”* ይላሉ ዶ/ር ዕቆብ በመጥሀፋቸው።

የአፋር ህዝብ የበላይ ጠባቂና አባት የሆኑት ክቡር ቢተወደድ አሊ ሚራህ ለዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ በሰጡት ቃለ ምልልስ፤ *“የአፋር ህዝብ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ አገሩን ወዳድ ነው በታሪኩና በባህሉም ይኮራል። ኢትዮጵያዊነታችንም ማንም ሊነፍገን አይችልም የ አፋር ህዝብ ጠላቶች ብቻ ናቸው አፋርን የተለየች አድርገው የሚቆጥሩት። እነኚህ ፀረ ህዝቦችን እናጋልጣቸዋለን ይህም ለኢትዮጵያ ህዝብ ሲባል መደረግ አለበት”* ማለታቸውን ‘አሰብ የማን ናት?’ መጥሀፍ ካወጋን በኋላ አያይዞም፤ *“…ክቡር ቢተወደድ አሊ ሚራህ በሐምሌ ወር 1983 ዓ/ም ኢህአዴግ የሽግግር መንግሥት ለማደራጀት በጠራው ጉባኤ ላይ ተገኝተው አቶ መለስና አቶ ኢሳያስ ባሉበት ‘የአፋር ህዝብ ወሰን ቀይ ባህር ነው። ግመሎቻችን እንኳን የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቁታል’ ብለው ነበር።…”* በማለት የታሪክ መረጃዎችን ደርድሯል። (አፅንዖት የቃኚው)

አስቀድመን እንደጣፍነው የነፃነት ጎህ ሲቀድ 614 ገጦች ያሉት ግዙፍ መጥሀፍ ነው። በዚህ ውስጥ ያልተተነተነ ፖለቲካዊ ቲዎሪ ለማግኘት ይከብዳል። ህወሃት በመንግሥትነት አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ በኢትዮጵያ ላይ ባሳረፈው የመጀመሪያው ሰይፍ - ሀገሪቷን ወደብ አልባ በማድረግ አሰብን ‘ለወንድም’ ኢሳያስ በ1983 ዓ/ም በፊርማ ማስረከብንም ሆነ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ካበቃ በኋላ ባንዳው ህወሃት አሰብን “ለአንዴና ለመጨረሻ” ከ ኢትዮጵያ መነጠል በሚል እኩይ እሳቤ በአልጀርሱ ስምምነት ለኢትዮጵያ አትገባም በማለት ለኤርትራ ተሟግቶ ባስረከበበት መንገድ - ላይ ግን ጠሀፊው አቋማቸውን በግልጥና በማያሻማ ቋንቋ ያሰፈሩበት አንድም መስመር አለመኖሩ እጅግ የሚከነክነን ሆኖ ይገኛል።

በህወሃት ውስጥ ስላለው የግራ ርዕዮት፤ ስለ ሊብራልና አብዮታዊ ዲሞክራሲ፤ ስለ ኢኮኖሚ፤ ስለ ዘውግ፤ ወዘተ…ወዘተ…በአያሌ ገጦች በተነተኑበት መጥሀፍ ይህንን ቁልፍ የ ኢትዮጵያውያንን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄ - የአሰብን ጉዳይ - እንደ ኢኮኖሚስትነታቸውም ሆነ እንደ ፖለቲካ ተንታኝነታቸው ፋይዳውንም ሆነ ችግሩን በማስቀመጥ በግልጥ ያሰመሩት የአቋም መስመር ከቶም የለም። ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ዓላማ ስለ ኤርትራ የአገነጣጠል ሁኔታና ስለ አሰብ ወይም ስለ ኢትዮ ኤርትራ ጦርነትና ስላስከተለው መዘዝ መፃፍ አልነበረም ልንባል እንችል ይሆናል። መልካም። ይሁንና ግን የወቅቱን ሀገራዊ በደል ለትውልድ የማቅረብም ሃላፊነት የነበረበት ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ስለ

ኢህአዴግ ሊብራላዊ ወይም አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊነት ወዘተ ሰፊ ትንተና ሲሰጠን አስቀድሞ ያነሳነውን አንገብጋቢ ሀገራዊ ጥያቄ እንደምን አንድ ምዕራፍ እንኳን ሰጥቶ በአግባቡ ማስተናገድ አቃተው? ብለን መጠያቃችን ግን አግባብ ይሆናል።

አስቀድሞ ከመጥሀፉ እንደተመዘዘውና የአሰብን ጉዳይ በተመለከተ ካሰፈሩዋቸው ጥቂት አንቀፆች (ወደፊት) እንደምንረዳው ሀሳባቸውን የገለፁልን በሶስተኛ መደብ (በተመልካችነት) ወይም ደግሞ ገለልተኝነት በሚንፀባረቅበት የታሪክ ዘጋቢነት  አጠቃቀም ሆኖ ይገኛል።

እየህ ላይ አንባቢያን አበክረው እንዲረዱልኝ የምሻው ዋናው ነጥብ የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ አይደለም። ጥያቄው፤ ግንጠላው የተካሄደበት መንገድ በግንጠላውም ህወሃት አሃዱ ብሎ በጀመረው የመንግሥትነት ርምጃው የኢትዮጵያን ህዝብ ድምፅ ወይም ብሄራዊ መብት መቀርቀቡ/መርገጡ፤ በሀገራችን ጊዜያዊም ሆነ ዘላቄታዊ ጥቅም ላይ በዚህ ቅኝት ሊገለፅ የማይችል (ከስፋቱ አኳያ) ጉዳትና መዘዝ የሚያስከትል/ያስከተለ መሆኑን፤ ወዘተርፈ **በማንሳት የህወሃትንና ሻዕቢያን የኢትዮጵያን ካርታ ሸንሸና የተቃወሙትን ኢትዮጵያውያን አቋም እንኳን በመደገፍ ራሳቸውን ከዚህ ጎራ በ"እኛነት" አለመከተታቸው ነው።** እሳቸው **"የ ኢትዮጵያ ብሄረተኞች"** በሚል ለገለፁዋቸው ህወሃት **"ነፍጠኞች"** የሚል መጥሪያ አለው። ይህ ከገረምን አይቀር የሚከተለውን እንጨምርበት።

*"ኢህአዴግ የኤርትራን መገንጠል ለማወቅ የመጀመሪያ መሆን ብቻ ሳይሆን በቶሎ እስክትገነጠልለት ድረስ መጠበቅ ያቃተው እስኪመስል ድረስ፤ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ከግምት አለማስገባት ወዘተ ተዳምሮ ኢትዮጵያውያን የኢህአዴግን አቋም **አልወደዱለትም** ለማለት ይቻላል።"* ገጥ 123 (አፅንዖት የኔ)

ልብ በሉ። "ኢትዮጵያውያን አልወደዱለትም ለማለት ይቻላል" እነጂ ያሉን "አልወደድንለትም" አላሉንም። እንዲህ ያለውን የሀገርንና የህዝብን መፃኢ ህልውና ሊፈታተን በሚችል ግዙፍ መሰረታዊ ጥያቄ ላይ እሳቸው 'በመውደድ' እና 'ባለመውደድ' አገላለፅ እንጂ ያለፉት በመቃወምና በማውገዝ ወይም በታሪክም ሆነ በህግ አንጣር የግንጠላውን ሂደት በማበራየት አቋማቸውን አላስቀመጡም። ኤርትራን ከማስገንጠል ጋር አሰብን በእጅ መንሻነት ወዲ ዜናዊ  ለኢሳያስ አፈወርቂ መሸለሙ ያሳሰባቸውም አልነበረምና። ይሁንና ህወሃትና ህወሃት የመራው ጉባኤ ኤርትራ የኢትዮጵያን የባህር በር አጠቃልላ እንድትገነጠል ማድረጉ በወንጀለኝነትም የሚያስጠይቅ ሆኖ ይገኛል።

ይህ የህወሃት ዕኩይ ተግባር በወንጀለኛነት የሚያስጠይቀው መሆኑን ከበርካታ ዓለም ዐቀፍ ህግጋትና ከኢትዮጵያ ህገመንግሥት አንጣር ብጥርጥር አድርገው "አሰብ የማን ናት?" በሚለው መጥሀፍ ለትውልድና ለታሪክ ካስቀመጡት የዶ/ር ያዕቆብ ዘገባ የሚከተለውን ልብ ይሏል፤

*"ኢትዮጵያ ለኤርትራ ዕውቅና ለመስጠት የመጀመሪያ አገር ስትሆን ከዚያም አልፋ ለተባበሩት መንግሥታትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኢትዮጵያ ዕውቅና መስጠትዋን ስታስታውቅ **በመጀመሪያ በሠላም ጉባኤው ቀጥሎም በሽግግር መንግሥቱ የተለያዩ የ ኢትዮጵያ ህግጋት ተጥሰዋል።** ኤርትራን ማስገንጠል በጊዜው የነበረው የደርግ ህገ መንግሥትን የሚጥስ ቢሆንም የደርግ ሥርዓት ሲደመሰስ የሥርዓቱ መሰረት የነበረው ህገ መንግሥትም ተደምስሶ ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ሌሎቹ  የአገሪቱ ህግጋት እንደነበሩ ሲሆኑ በተለይም በ1949 ዓ/ም የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በጉባዔው ወቅትም ያገለግል እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይኸው ህግ **ጥቂት ለውጦች ተደርገውበት እያገለገለ** ነው። የኢትዮጵያ አካል የነበረችውን ኤርትራን ማስገንጠል የዚሁ የወንጀል ህግ ቁጥር 253 የሚፃረር ነው።"* ይላል 'አሰብ የምን ናት?' መጥሀፍ። (አፅንዖት የቃኚው)

ለመሆኑ ዛሬ ድረስ ኢህአዴግ የሚገለገልበት የ1949 ዓ/ም የሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ድንጋጌ መካከል ህግ ቁጥር 253 ምን ይላል? 'አሰብ የማን ናት?' መልሱንም አስቀምጦልናል - እንደሚከተለው።

**አንቀፅ** 253፤ *"ማንም ሰው የህዝብን የአንድነት ህብረት እንዲፈርስ የሚያደርግ ተግባር በመስራት ወይንም ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት አገር ወይም ህዝብ ከፌዴሬሽኑ ተከፍሎ ወደ ሌላ መንግሥት ሥርዓት ህገ ወጥ በሆነ በማናቸውም ሁኔታ ይህን የመሰለ ተግባር ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ለሚደርስ በሚችል ፅኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ ከሆነ በሞት ፍርድ ይቀጣል።"*

እነሆ ህወሃት/ኢህአዴግ ባልፈረሰውና በመጠነኛ መሻሻል (ምናልባት ንጉሠ ነገሥት የሚለውና ተመሳሳይ ቃላት ወጥተው) እራሱ ዛሬ ድረስ በሚገለገልበት የ1949 ዓ/ም የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት አሰብን ጨምሮ ኤርትራ እንድትገነጠል በማድረጉ በወንጀለኝነት ይጠየቅበታል። የህወሃት አሰብን መርቆ ኤርትራን መገንጠሉን 'የኢትዮጵያ ህዝብ አልወደደለትም ማለት ይቻላል' የሚለው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' አባባል ከዚህ ነባራዊ እውነታ አንጻር ይህንን የታሪክ ክህደት ዛሬ ላለውም ሆነ ለመጪው ትውልድ በሚገባና በጠራ ቋንቃ አለማስቀመጡ ብቻ ሳይሆን ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ የህወሃት/ኢህአዴግን ህገወጥ ፀረ ኢትዮጵያ ተግባር አምርሮ የተቃወመ እንጂ ምናልባትነትን በተላበሰ የጥርጣሬ እግረ መንገድ ገለፃ 'ህዝብ አልወደደለትም ነበር ማለት ይቻላል' ተብሎ በድፍኑ የሚታለፍ ከቶም አይደለም።

ቀጣዩን ደግሞ ያስተውሏል፤ ከ'የነፃነት ጎህ ሲቀድ'

*"ኢህአዴግ ከኤርትራ ጋር በተያያዘ ሀገሪቱን ወደብ አልባ ማድረጉና የወደብ ጥያቄን እንደ አልባሌ መሬት የማግበስበስ ጥያቄ አድርጎ ማየቱ፤ ይህንንም በተለያየ ዲስኩር ለህዝብ በግልፅ ማቅረቡ አልተወደደለትም ነበር።"* ገጥ 123 (አፅንዖት የኔ)

ኢህአዴግ'ኮ ጫካ ሆኖ የነገረንን ነው አዲስ አበባ ሲገባ የፈጠመው። ያልነገረንን፤ ያላስጠነቀቀንን አላደረገም፤ ህወሃታዊ ቃል ኪዳኑን ጠብቆ ፈጠመ እንጂ። ቃል የእምነት ዕዳ መሆኑን ተግብሮ አሳየን እንጂ። ህገ ወጥ ተግባሩንም ህጋዊ ነው ብሎ በግልጥ አደባባይ ቀርቧል። በኢትዮጵያ ህልውና እና የግዛት ሉዓላዊነት ያገባናል የሚሉ ፖለቲከኛ ምሁራን ሃላፊነት ደግሞ በህዝብና በሀገር ላይ ኢህአዴግ/ህወሃት የፈጠመው ህገ ወጥ ተግባር ህጋዊ ላለመሆኑ ህገ ወጥነቱን ማሳየትና ማበራየት መሆን አይገባውምን? ከዚህስ በላይ ትኩረት ሊሰጠውና ብዙ ገጦች ሊጣፍበት የሚገባው ጉዳይ አለን? የነፃነት ጎህ ሲቀድ የህወሃትን ጋጠ ወጥ ዘረኛና ማን አለብኝ ትምክህት ባነሳነው ህጋዊ ጥያቄ አንጻር በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ ሲደቁሰው ፈጥሞ አናይም፤ ከገለልተኛ አስተያየት በተቀር። ለምን? ብለን መጠየቅ ደግሞ መብታችን ነው፤ የእኛ ታሪክ ለእኛው እስከቀረበልን ድረስ።

እንደው ለመሆኑ 'ያልወደዱትን' ምን ያደርጉታል? ብለን እንጠይቅ። አጭር ነው መልሱ። ይርቁታል። ይሸሹታል። ይንቁታል። ታዲያስ? "…ኢህአዴግ ሀገሪቷን ወደብ አልባ የማድረጉን…ዲስኩር አልተወደደለትም ነበር" ሲለን 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ምን ማለቱ ይሆን?

አለመውደድ'ኮ ስሜት ነው። ስሜትንም ይገዙታል። አሰብ ለኢትዮጵአውያን የስሜት ጥያቄ አይደለም። ከቶም። አሰብ ለኢትዮጵያውያን በመሞትና በመዳን መካከል ያለ የህልውና ትንቅንቅ ጥያቄ ነው። አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል ይላል የአረጋውያን

ብሂል። የኢትዮጵያን አፍንጫ ረግጦ አሰብን ከአካሏ በመሰየፉ ደም እንባ እያነባች ትገኛለች ኢትዮጵያ። ይህ ህመም የአለመውደድን ስሜት አይፈጥርም። ይህ የቃላት ስንጠቃ አይደልም። ይህ የፖለቲካ ቁማርም አይደለም። የመርህ ጥያቄ ነው። የሉዐላዊነት ጥያቄ ነው። ይህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ቀዳሚው ጥያቄ ነው።

የአሰብን ጉዳይ ኢትዮጵያውያን የምንንቀው፣ የምንሸሸው፣ የምንርቀው ስሜት አይደለም። ህመም ነው። ታመናል። ድፍን ጦቢያ ታሟል። ኢትዮጵያ ታማለች። ከህመሟም መዳን ግድ ይላታል።

ኢህአዴግ ሊያክማት አይችልም። የጣዕር ዘመኗን አርዛሚ የእንግዴ ልጇ ነውና። በ ቁስሏ እንጨት የሰደደ። ለዚህ ተግባሩም እፍረተ ቢስ ነውና በድፍረትና በትዕቢት እንደ ዠግና እንደ መሲህ በአደባባይ ፏልላል፣ ይፏልላልም።

ኢህአዴግ ላላፈረበት ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ስለምንድን ነው ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ይህን ህመማችንን በስሜት መግለጫነት ብቻ አኮስሶና አሳንሶ በታሪክ ሰነድነት ያቀረበልን? ስለምንድን ነው የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ልክ ላለመሆኑ ልክ ልኩን በመልስ ምት በታሪክና በህግ አስረግጦ ያላቀረበልን? ወይስ ኢትዮጵያ አሰብን ማጣቷ ህመሟ ሳይሆን ‘የ አለመውደድ’ ስሜቷ ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ ይሆን - ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ጠሀፊ።

ኢትዮጵያ በኢህአዴግ አካሏን አሰብን በመሰየፏ የደረሰባትን ህመም ጥልቅት ከመረመረው ‘አሰብ የማን ናት?’ መጥሀፍ የሚከተለውን እናገኛለን፣

*“…ኢህአዴግ በ1983 ዓ/ም በኢትዮጵያ ሥልጣን ከመያዙ በፊት አስር ሳንቲም መክፈል ቀርቶ እንዲያውም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ለነበረው የወደብ አገልግሎት ዛሬ አገሪቱ በቀን ከሶስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ለጅቡቲ ትከፍላለች። ይህ ለወደብ የሚከፈለው በጣም ከፍተኛ ገንዘብ ውሃ እንደበላው የሚቆጠር ነው። ምክንያቱም በለውጡ ኢትዮጵያ የምታገኘው ዕቃም ሆነ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም የለምና። ይህም ማለት ድህነትን ለመቅረፍ ሊረዱ ይችሉ የነበሩ በየዓመቱ ሃያና ሰላሳ ፋብሪካዎች ሊገነባ የሚችል ወይንም መጠነ ሰፊ ለሆነ መሰረተ ልማት ግንባታ ሊውል ይችል የነበረ ገንዘብ በህወሃት መሪዎች የዲፕሎማሲና በሌሎች ሌሎችም ድክመቶች ምክንያት ይህንን ሁሉ ገንዘብ ለጅቡቲ ትገብራለች።”* በማለት ሀቁን ካፍረጠረጠ በኋላ ትንታኔውን በሰፊው ይቀፅልና፣

*“እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ አገሮች ከዋና ዋና የገበያ ማዕከሎች የተገለሉና ከገበያ ማዕከሉ የራቁ ሲሆኑ ወደብ አልባነት ለኢኮኖሚ  እድገታቸው ከፍተኛ ማነቆ ሆኖባቸዋል።…ዶ/ር አክሎግ ቢራራ (ኤ ኬዝ ፎር ላንድሎክድ ካንትሪስ) በቅርብ ጊዜ ከሳሃራ በታች የሚገኙ አገራት የተደረገ ጥናት ሲጠቅሱ ከሳሃራ በታች የሚገኙ ወደብ አልባ አገራት የውስጥ ለውስጥና ወደ ወደቡ የሚያሸጋግረው የትራንስፖርትና ተያያዥ ወጪዎች ወደብ ካላቸው አገራት በአራትና በአምስት እጅ እንደሚበልጥ ይገልፃሉ። ይህም ከእቃው ሽያጭ የሚገኘው አብዛኛውን ገንዘብ ይወስድባቸዋል ማለት ነው። ይህም ማለት ኢ ትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸው ምርቶች ዋጋቸው ስለሚንር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ አይችሉም። እንዲሁም ወደ አገር የሚገቡ ሸቀጦች  ዋጋቸው በጣም ከፍ ይላል። ይህም በመሆኑ የገዢው ፓርቲ የአሰብ ወደብ ለኤርትራ በማስረከቡ የአገሪቱ ደህንነትና እድገቷ በከፋ ሁኔታ ላይ ጥሏል ማለት ነው።*

*“በ2008 ዓ/ም (እአአ) በዓለም 44 ወደብ አልባ አገሮች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ ሰላሳ አንዶቹ ድሃ ሲሆኑ አስራ ሶስቱ ደግሞ የድሃ ድሃ የሚባሉ ናቸው። አስራ ሶስቱም የድሃ ድሃ አገሮች አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ኢትዮጵያም ከእነዚሁ አስራ ሶስቱ ድሃ አገሮች ተርታ*

*ትሰለፋለች።"* በማለት 'አሰብ የማን ናት?' ኢትዮጵያ አሰብን እንድታጣ በመደረጓ የደረሰባትን እጅግ ጥልቅ ህመም በመመርመር ማስረጃውን በማስፋፋት፤ የኢኮኖሚ ሊቅ ፖል ኮልየር "የመጨረሻዎቹ ድሃ ቢሊዮኖች" በሚለው መጥሃፋቸው ያሰፈሩትን እውነታ ያጣቅሳል - እንደሚከተለው፤

*"ድሃ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ወደብ አልባ አገሮች ከአራቱ የልማት ማነቆዎች በአንዱ (በወደብ አልባነት) ተጠፍረው የተያዙ ናቸው። የባህር በር ካለህ ገበያህ መላው ዓለም ነው። የባህር በር ከሌለህ ደግሞ ገበያህ የጎረቤት አገር ብቻ ነው።...**ወደብ አልባ አገሮች የጎረቤቶቻቸው እስረኞች ናቸው።"*** (የጥቅሶቹ አፅንዖት የቃኚው)

እነሆ የጦቢያ ህመም ደረቅ ሀቅ!! 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ሊነግረን፤ ለዘክረን፤ ውስጣችንን ሊያንጠን፤ ለፍንዳታ ሊያብላላን...ይገባ የነበረው የኢህአዴግን ፕሮፓጋንዳ "አለመውደዳችንን' ሳይሆን የህመማችንን ደረጃ ልክ በማበራየት ሊሆን ይገባ ነበር።

አንባቢ ሆይ! 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የአሰብን ጥያቄ በአግባቡ አስተናግዶ የኢትዮጵያ ህዝብም አሰብን በግፍ በመነጠቁ የተሰማውን ውስጣዊ ቁጭትና ብግነት በአግባቡ ለትውልድና ለታሪክ ያልዘገበ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዘመን በህይወት ላለነውና ሁኔታውን ለምናውቀውም በታሪክነት የተዘገበልን 'የአለመውደድ' ታሪክ ከነባራዊው እውነታ አንጻር ይበራይና ይፍረጠረጥ ዘንዳ ግድ በመሆኑ ነው በስፋት አቀርብ ዘንዳ መገደዴ።

ለመሆኑ በአሰብ ዙሪያ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የኢህአዴግ ፕሮፓጋናዳ 'አልተወደደለትም ነበር' ሲል የዘገበልን ምን ይመስል ነበር? እነሆ አብነት ከ'አሰብ የማን ናት?'

*የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ...የባህር በር ለአንድ አገር እድገት ምንም የሚጫወተው ሚና እንደሌለ በመግለፅ የሚከተለውን ብለዋል፤*

*"...አሁን የአሰብንም የምፅዋንም ወደብ አንጠቀምም። እነዚህ ወደቦች ባለመጠቀማችን ምንድን ነው የቀረብን ነገር የለም። ልማት ቢሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ልማት፤ ፈጣን ልማት የተመዘገበው በአለፉት አራት ዓመታት ነው። ስለዚህ ወደብ አለመኖሩ እረሃብ አያመጣም። በጎረቤት አገር ወደብ በመጠቀም መሥራት ይቻላል።...**ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለ ወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበት የምናዝንበት ምክንያት የለም። ወደብ አለመኖሩ አይጎዳንም፤ ሊጎዳንም አይችልም።...ስለዚህ ወደብ ለማደግ አስፈላጊ አይደለም።"***

ይህ የኢህአዴግ ቁንጮ ፕሮፓጋንዳ አስቀድመን ካቀረብነው (አሰብ የማን ናት?) መረጃዎች አንጻር የጨለማና የብርሃንን ያህል ልዩነት አለው። በቀን ሶስት ሚሊዮን ዶላር የምትደማው ሀገራችን ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ምን ያህል 'ውሃ የሚበላው' የደም ወጪ ስትገብር ኖራለች ብለን ብናሰላ ምናልባት ህሊናችንን እስከ መሳት ሊያደርሰን ይችላል። ይህ ዕደገት ነው ወይስ በኢትዮጵ ህመም ጣዕር መሳለቅ? እንዲህ ያለውንስ ግብዝ ፕሮፓጋንዳ በልዝብና ክብደት በሌለው 'አለመውደድ' ስሜት አቅልለን ነው መግለጥ ያለብን ወይስ በማውገዝና በመኮነን እውነታውን ይፋ በማድረግ? እናንተው ፍረዱ።

አያሌ የኢኮኖሚ፤ የታሪክና የፖለቲካ ጠበብት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ህወሃት/ኢህአዴግ ኤርትራ አሰብን ጨምራ እንድትገነጠል ካደረገበት ጊዜ ዠምሮ እጅግ በርካት ጥናታዊ የሆኑ ጂኦ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ትንታኔዎችን ያዘሉ ጥሁፎችን በተለይ ዛሬ በታገዱት የኢትዮጵያ ነፃ ሚዲያ ተቋማት ላይ በማውጣት ዕውነታውን ከህወሃት ሸፍጥ እያበራዩ ለህዝብ አቅርበዋል፤ ዛሬም (በውጪው ዓለም በሚገኙ ሚዲያዎች) እያቀረቡ ይገኛሉ። ከየህ በተጨማሪም በተለያዩ ሚዲያዎች በሰጡትና

በሚሰጡት ቃለ ምልልሶች የአሰብ ጥያቄ ‘የመሬት ማግበስበስ የነፍጠኞች ጥያቄ’ አለመሆኑን በህግና በታሪክ እያስረገጡ ሲያሳውቁ ኖረዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ። በኤርትራ ግንጠላ እና በአሰብ ወደብ ጥያቄ ዙሪያም ለትውልድና ለታሪክ የሚቀሩ መጣህፍቶችንም ያበረከቱልን በርካቶች ናቸው፤ ወደፊትም ይኖራሉ። ይሁንና ለዚህ ቅኝት ማበራያ እንዲሆን የመረጥኩት ‘አሰብ የማን ናት?’ የሚለው መጥሀፍ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ምሁራንን እና የውጪ ሀገር ጠሀፍትን ሥራዎች ያጣቀሰ በመሆኑ ስለሆነ ከላይ በደምሳሳው ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ ያለምንም ተቃዋሚ ማብራሪያ ህወሃታውያኑ ያሉትን ብቻ ያስቀመጠልንን ታሪክ አስመልክቶ ጥያቄው የመሬት ማግበስበስ ሳይሆን የይገባናል የባለቤትነት ህጋዊና ታሪካዊ ጥያቄ ስለመሆኑም ጭምር ለአንባቢያን ተጨማሪ ግንዛቤ ይረዳ ዘንዳ የሚከተለውን ከ’አሰብ የማን ናት?’ ለመንቀስ ተገድጃለሁ።

*“ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንደነበረች በመጀመሪያ የታወቀው ከ100 እስከ 150 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተፃፈ በሚገመተው በ’<u>ፒሪፕለስ ኦቭ ዘ ኤርትሪያን ሲ’</u> በተሰኘው መፅሀፍ ነው። ይህም መፅሀፍ የአክሱም መጠነ ሰፊ ንግድ በዋነኛው የባህር በሩዋ በአዱሊስ በኩል ይተላለፍ እንደነበር አትቷል። ቀጥሎም ‘ኮስሞስ’ የተባለ ሰው በፃፈው የ’<u>ክርስቲያን ፎቶግራፊ’</u> በሚለው መፅሀፍ አዱሊስን መጎብኘቱንና በጊዜው የነበረው ንጉሠ ነገሥት አፄ ካሌብ እንደነበር አፄ ካሌብም እጅግ የዳበረ የባህር ሃይል እንደነበረው ቀይ ባህርንም ተሻግሮ የመንንና ደቡብ አረቢያን ይቆጣጠር እንደነበር ፅፏል።*

*“የአክሱም መዳከምና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ሥልጣን ላይ መውጣት ኢትዮጵያን የባህር በር አላሳጣትም ነበር። ነገሥታቱ በቀጥታም ይሁን ወይም በጥገኞቻቸው አማካይነት የቀይ ባህር ወደቦችን ይቆጣጠሩ ወይንም ይገለገሉ ስለነበር አክሱም ሙሉ ለሙሉ ከቀይ ባህር የተገለለችበት ጊዜያት ጥቂት ነበር ማለት ይቻላል።”* በማለት የነበረውን ታሪካዊ አመጣጥ ያስቀምጥልንና ከዘመን በኋላ ቱርኮች ፤እንግሊዞች፤ ጣሊያኖች በቀይ ባህር አካባቢና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍሎች የነበሩዋቸውን እንቅስቃሴዎችና ይዞታዎች ‘አሰብ የማን ናት?’ በሰፊው ካተተ በኋላ ታሪኩን ሲቀጥል፤

*“ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትም በታሪክ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከቀይ ባህርና ከ ኤደን ገልፍ ትዋሰን እንደነበር (ኢሚጅ ኦቭ ኢትዮፒያ ኦቨር ሴንቸሪስ - በተባለው ፅሁፍ) ሲያረጋግጡ ይህም ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንደነበረች አንድ ሌላ ማስረጃ ነው።… የአፋር ተወላጅ የታሪክ ፀሀፊ (ሻህ ጁማለዲን ኢብራሂም ኻሊል ኡሻሚና በልጃቸው ሃሺም ጃማለዲን ኢብራሂም ኡሻሚ ዶ/ር የተፃፈ -የአፋር/ደናኪል ታሪክና መረጃ አርኪ ምንጭ) ስለ አፋር ህዝብ ታሪክ ሲፅፉ በ16ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዙሪያ የበላይነቱን ይዛ እንደነበርና ሰፊም ይዞታ እንደነበራት የአንድ በአረብኛ የተፃፈ ካርታ ያረጋግጣል ብለዋል። ፀሀፊው ካርታውን ሲጠቅሱ፤*

*“…ካርታ ቁ.3/4(ለ) በአረብኛ የተፃፈ ካርታ ነው። በዚህ ካርታ ላይ ‘ኢትዮጵያ’ ተብሎ የተሰየመው ግዛት በቀይ ባህር ዙሪያ ያሉትን የቤጃ ህዝቦች ምድር፤ የሃባብና የበለው ህዝቦችን ምድር እንዲሁም በአፋር ግዛት ከዳህላክ ደሴቶች እስከ ዘይላ ድረስ ያለውና ከዚያም ያለው የሱማሌን ግዛት ያጠቃልላል ሲሉ ፅፈዋል።…ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም…(የክህደት ቁልቁለት በተሰኘው ፅሁፋቸው) በምሳሌነት የአፄ አምደ ፅዮን /1312-1392/፤ የአፄ ገላውዲዎስ /1533-1551/፤ የአፄ ሠርፀ ድንግል 1555-1587/ እና ሌሎችም ዜና መዋዕሎችን በማመላከት የኢትዮጵያ የምሥራቁ ወሰን ቀይ ባህር እንደነበር ገልፀዋል።”* በማለት አሰብ የኢትዮጵያ ለመሆኗ ታሪካዊ መረጃዎችን በስፋትና በጥልቀት አስቀምጧል - ‘አሰብ የማን ናት?”። በዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ የአሰብ ባለቤትነቱን መጠየቁ የመሬት ማግበስበስ ጥያቄ ሳይሆን የይገባናል የመብትና የባለቤትነት ጥያቄ ሆኖ ይገኛል እንጂ የባንዳዎችን ህገ ወጥ ዲስኩር በመውደድና ባለመውደድ ላይ ያለ የስሜት

መለኪያ አልነበረም፤ አይደልም። አሰብን በወደብነት የገነባቻትና ህይወት የዘራችባት ኢትዮጵያ ስትሆን ለዚህም እስከ 3 ቢሊዮን ዶላር ወጪ አድርጋለች። የተለያዩ ምንጮችን ያካተተው 'አሰብ የማን ናት?' እንደሚከተለው አንጥቧል፤

*"አሰብ ከኢትዮ-ኤርትራ ፌዴሬሽን በፊት እዚህ ግባ የማይባል ጥቅም ብቻ የምትሰጥ ማንም ትኩረት ያልሰጣት ትንሽ ወደብ ነበረች። የተሟላች ወደብ ሆና ማገልገል የጀመረችው ከአርባ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ እጅ ከገባች ወዲህ ነው። የኢትዮጵያና የ ኤርትራ ፌዴሬሽን እንደፈረሰ አሰብን በሰፊው መገንባትና ማሻሻል ተጀምሮ በመጀመሪያ ሞግራድ በሚባል የዩጎዝላቪያ ኩባንያ ሥራው ሲጠናቀቅ ለዚህም ሥራ 28 ሚሊዮን ብር በዛሬው ተመን ምናልባት ከ260 ሚሊዮን ብር በላይ ኢትዮጵያ ወጪ አውጥታለች።"* በማለት ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ የፃፉትን በማጣቀስ ካቀረበልን በኋል አያይዞም፤

*"በደርግ አገዛዝ ዘመንም ወደቡ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጎለት እንደነበርና ለዚህም ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ ለአሰብ ግንባታ እስከ 3 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንዳደረገች በ አንድ ወቅት የአሰብ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ጌታቸው በቀለ ለዚሁ ፀሀፊ ገልፀውለታል።...ኢትዮጵያ በአሰብ ከተማ የተለያዩ የመንግሥት ህንፃዎችን፣ መንገዶችን፣ ተማሪ ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና መርከብ ማሳረፊያዎችን አሰርታ ነበር። ለእነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ወጪ ያወጣች ሲሆን ለዚህ ሁሉ ንብረት ኤርትራ አሰብን ስትወስድ ቤሳ ቤስቲኒ ለኢትዮጵያ አልከፈለችም። እንዲያውም አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት እስከ ዛሬ አሰብን በነፃ ለተጠቀምንበት ኤርትራውያን ሂሳብ እናወራርድ እንዳይሉን ስጋታቸውን ገልፀዋል። አሰብ ከፌዴሬሽኑ በኋላ በተደረገላት መሻሻል ትልልቅ መርከቦችን ለማስተናገድ ችላ ለመኻሉና ለደቡብ ኢትዮጵያ የባህር በር ሆና ታገለግል ነበር።*

*"ወደቡ ከነበረበት በጣም አድጎ ኢትዮጵያ ለቅቃው ስትወጣ በግምት 2.8 ሚሊዮን ቶን ጭነት ሊያስተናግድ የሚችል አቅም ነበረው።...አሰብ ዘመናዊ ከተማ ስትሆን በውስጧም ብዙ መስጊዶችና ቤተክርስቲያናት፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የህዝብ መገልገያዎች፣ የተሟሉ መንገዶች ሲኖሩዋት፣ ከኢትዮጵያም ጋር በአስፋልት መንገድ ተያይዛለች። የ አሰብ ወደብ...ሰባት ትልልቅ መርከቦች ሊያቆም ሲችል ባህረ ሰላጤው በጣም ትራፊክ ከሚበዛባቸው የዓለም ባህረ ሰላጤዎች አንዱ ነው። አብዛኛዎቹ በቀይ ባህር በኩል አድርገው የሚያልፉ መርከቦች በአሰብ በኩል አድርገው ሲሆን በዓመት ወደ 20.000 የሚጠጉ መርከቦች 7.000 ሚሊዮን (ሰባት ቢሊዮን) የሚጠጋ ጭነት ይዘው ይጓዛሉ።"* በማለት የተለያዩ ምንጮችን አጣቅሶ አስቀምጧል፤ 'አሰብ የማን ናት?'።

ኢትዮጵያ አንጡራ ንብረቷን አፍስሳ የገነባቻትንና ከጥንት ከመሰረቱ ዠምሮ የ ኢትዮጵያ አካል የሆነችውን አሰብን የኤርትራ ጠበቆች ባንዳዎቹ የህወሃት መሪዎች የ ኢትዮጵያን ህዝብ ህጋዊና ታሪካዊ የይገባኛል ጥያቄ 'የመሬት ማግበስበስ የነፍጠኞች ጥያቄ ነው' ማለታቸውን 'ህዝቡ አልወደደለትም ማለት ይቻላል' ተብሎ የሚታለፍ የእግረ መንገድ አስተያየት ሊሆን ከቶም አይገባም። በመሰረቱ 'በአለመውደድ'ና 'በመቃወም/በማውገዝ' መካከልም የሰማይና የመሬትን ያህል ርቀት የያዘ የፅንሰሀሳብ ልዩነት አለ። በሁለቱ 'በ አለመውደድ' እና 'በመቃወም' መካከል ያለው ልዩነትም እንደዋዛ የሚታለፍ ሊሆን የማይገባው በመሆኑ ነው አስቀድመን የነቀስነውን ሰፋ ያለ ዝርዝር መጥቀሳችን።

እንቀፅል፤ ከ'የነፃነት ጎህ ሲቀድ'፤

*"ይህ መንግሥት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም መጠበቅ ደንታ የለውም ወይም ደግሞ የብሄራዊ ጥቅም ምንነት ግልፅ አልሆነለትም በሚል ድርጅቱን በጥርጣሬ የሚያዩ ቁጥራቸው ትንሽ አልነበረም።"* ገጥ 123

እነሆ በኢህአዴግ ላይ በዚህ መጥሀፍ ውስጥ በአብዛኛው እንደተንጠባረቁት የፖለቲካ አመለካከቶች ይህንንም አንቀፅ ስናነብ ገለልተኛ ወይም ታዛቢ የታሪክ ጠሀፊ የግራ ቀኙን አቋም የሚነግረን ወይም በዳኝነት የተቀመጠ ሰው ፍርዱን ለእኛ የተወልን እንጂ - ሀገራዊ የፖለቲካ ምሁር ስለ ሀገሩ አንገብጋቢ ጉዳይ ፖለቲካዊ እይታውንና ግንዛቤውን የሚያስጨብጠን ሆኖ አይሰማንም። ቀጣዩን ደግሞ ልብ ይሏል - ከመጥሀፉ፤

*"በኤርትራ መገንጠል የተበሳጩ ብዙ ሀገር ወዳድ ሀይሎች ቢኖሩም ተጋዳላዮቹ በነበራቸው ጨዋነትና ሰው አክባሪነት ...አዲሶቹ ሃይሎች 'ቅኖች ናቸው' ከሚል **ባለማወቅ እንዳይሳሳቱ ለመርዳትም** ብዙ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ሰዎች ተቀላቅለዋቸው እንደነበር አይዘነጋም።"* ገጥ 118 (አፅንዖት የኔ)

እንደ ዕውነቱ ከሆነ ይህን አንቀፅ ባነበብኩት ቁጥር እጅግ በጣም የሚገርመኝ ብቻ ሳይሆን ስለመከረኛይቱ ኢትዮጵያና ስለተገፋው ህዝቧ መፃዒ ዘመን ሳሰላስልም ጭልም ይልብኛል። በእንደምን ያለ ስሌት ኢህአዴግ ያደረገው ወይም ሊያደርግ የተዘጋጀው 'ባለማወቅ በስህተት' ሊሆን ይችላል የሚል ግንዛቤና 'እንዳይሳሳት' የርዳታ ድጋፍ ሊቸረው እንደተቻለ መቼም ቢሆን መቼ የሚገለጥልኝ አይመስለኝም።

'ኢትዮጵያ ወደብ አያስፈልጋትም' በማለት የሚያስተዳድረውን ሀገር የኢኮኖሚ ቁልፍ በፊርማ አሳልፎ በማስረከብ ረገድ በዓለም የመንግሥታት ታሪክ የመጀመሪያው ሆኖ የተመዘገበው ኢህአዴግ/ህወሃት የመጀመሪያ አጥፊ ርምጃ ላይ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ከ614 ገፆቹ ውስጥ እነሆ የአንድ ገፅ ተኩል የ'እግረ መንገድ' ገለፃ ሰጥቶ በ'እናንተው ፍረዱ' ገለልተኛነት ደምድሞታል።

ለመሆኑ ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣ ዠምሮ በተለያዩ ጊዜያት በተቃውሞ አደባባይ የወጣው የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢትዮጵያዊነቱ መግለጫ ባንዲራውን ከመልበስና ከፍ አድርጎ ከማውለብለብ ሌላ ህገ ወጥ የሆነውን የኢህአዴግን ካርታ ተቀብሎና ከአናቱ በላይ ይዞ አደባባይ ወጥቶ ያውቃልን?

በስደት ተበትኖ የሚኖረው ኢትዮጵያዊም ሲያደርግ የኖረውና እያደረገም ያለው ብቸኛውን የኢትዮጵያዊነት ምልክቱን አረንጓዴ፤ ቢጫ፤ ቀይ ሠንደቅ ዓላማውን እያነገበ ህወሃት/ሻዕቢያን በአደባባይ ይቃወማል እንጂ ህገ ወጡን ካርታ አንግቦ ወጥቶ አያውቅም።

ኢትዮጵያን በየብስ አጥሮ የባህር በር በማሳጣት ህወሃት ሸንሽኖ ህወሃት ዕውቅና የሰጠውን የኢትዮጵያን ካርታ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መቀበሉ ወይም ዕውቅና መስጠቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ራስ ምታት አይደለም፤ ለኢትዮጵያውያን (በዚህ ትውልድም ሆነ በተከታታይ ትውልዶች) የአሰብ ጉዳይ አሁን ባለበት ይዞታ ያልተቋጨ ጉዳይ ነውና!! የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃትንና ጋሻ ጃግሬዎቹን ከጫንቃው ላይ አሽቀንጥሮ ሲጥል በአስፈላጊው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ የወደቡ ባለቤት የሚሆንበት ጊዜ እንደሚመጣ ከቶም ልንጠራጠር አይገባም። በህገ ወጥ መንገድ ያጣነውን ለማስመለስ በምንወስደው እርምጃም የማንም ጣልቃ ገብነት የሚያቆመን አይሆንም።

ዶ/ር ብርሃኑ ከቃሊቲ እስር ቤት ከተፈቱ በኋላ ሰንበት በሎ ወደ ሲድኒ አውስትራሊያ አቅንተው ነበር። ጋባዦቻቸውም በሲድኒ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ የስብሰባ ጥሪ

አድርገውለት ነበርና ነዋሪው ህብረተሰብ በስፍራው ሲገኝ እኔም ተገኝቼ ነበር። በዚያ ስብሰባ ላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለው ይገኝበታል።

ጠያቂ፦ "የነፃነት ጎህ ሲቀድ መለያው የኢህአዴግ ህገ ወጥ ካርታ ነው። በዚህ ህገ ወጥ ካርታ ውስጥ ቁልፍ ጥያቄ የሆነው የአሰብ ጉዳይ ይገኝበታል። የእርስዎ መፅሀፍ ይህንን ህገ ወጥ ካርታ ለምን መለያው አደረገ?"

ዶ/ር ብርሃኑ፦ "*መፅሀፉን እንደጨረስኩ ከእስር ቤት ያወጡልኝ ሌሎች ናቸው። ከዚያ በኋላ መፅሀፉን ያየሁት ታትሞ ነው። የመፅሀፉን ልባስ እኔ እንዲያ ይሁን አላልኩም። እኔ* **ብሆን ኖሮ የማደርገው በመፅሀፉ ጀርባ የወጣውን ፎቶግራፌን አለማውጣት ነበር።**" (አፅንዖት የኔ)

አንባቢ ሆይ! ይህ ከላይ የቀረበው ጥያቄና መልስ የተፈበረከ ቃል/ቃላት የሉትም። እነሆ እንደ እግር ውስጥ እሳት እየለበለበን ለሚገኘው በግፍ ለተዘረፍነው ወደብ /የአሰብ/ ጥያቄ ዶ/ር ብርሃኑ በሰጡት መልስ ከካርታው ይልቅ የእሳቸው ፎቶግራፍ መውጣትን ነበር ትልቅ ስፍራ የሰጡት። በካርታው መውጣት ላይም ቢሆን ትንፍሽ ያሉት ነገር አልነበረም። በዚህ ምላሽ ምን ተሰማኝ? እናንተ ምልልሱን ስታነቡት የተሰማችሁን አላውቅም፤ እኔ ግን ገረወይና ሙሉ በረዶ በአናቴ ላይ የለቀቁብኝ ነበር የመሰለኝ። ሰውነቴ ሲደነዝዝ፣ ደሜ ሲቀዘቅዝ ተሰምቶኛልና። በተለይ በመጨረሻው አረፍተ ነገር መልሳቸው ብዙዎች ሲስቁ እንደ ህልም ተሰምቶኛል - ቀልደኝነታቸውን በማድነቅ። ለቀረበላቸው ጥያቄ ስላቅ መልስ ስለሰጡ ይሆን የሳቁት?...ብቻ እንደ ደነዘዝኩ ስብሰባው አለቀና እንደ ደነዘዝኩ ወደ ሰፈሬ አዘገምኩ።

<u>ከእባብ እንቁላል ርግብ ይወለዳል</u>

*"ኢህአዴግ ከመሰረቱ በአመለካከትም ሆነ በተግባር በትግል ላይ እያለም ዲሞክራሲን በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የብሄር ብሄረሰብ ጥያቄና አፈታቱን በሚመለከት በኤርትራ ጉዳይ ወዘተ መሰረታዊ ችግሮች ያሉበት መሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ።" ገፆ 29*

ይህንን አባባል በተመሳሳይ ገፆ ወረድ ብሎ ከቀረበው ጋር እናነፃፅረው፤

*"ድርጅቱንና (ኢህአዴግን/ህወሃትን ማለታቸው ነው) የሚመራውን መንግስት እንደጠላት ማየት የበለጠ ሊያስበረግገው ይችላል። ይህ ደግሞ ለአገሪቱ ሠላምና መረጋጋት አይበጅም ከሚል ድርጅቱ ሲሳሳትም አውቆ ለክፋት አይደለም ካለማወቅ ሊሆን ይችላል የሚል በእኔ ግምት አዎንታዊ አመለካከት ነበረኝ።"* ገፆ 20 (አፅንዖት የኔ)

ኢዚህ ላይ ሁለት መሰረታዊ የሆኑ የመርህ /ፕሪንሲፕል ጉዳዮችን ማጤን ይገባናል።

1. ኢህአዴግ አለበት የተባሉት መሰረታዊ ችግሮች ለኢህአዴግ ችግሮቹ አልነበሩም ሆነውበትም አያውቁም። የጠራ የነጠረ በኢትዮጵያ ላይ ያለው ፖለቲካዊ መርሃግብሩ ወይም የማያወላዳው አቋሙና መመሪያው እንጂ።

የኢህአዴግ ሾፌሮች ወይም የህወሃት የፖሊት ቢሮ አባላት ጥቁር መጋረጃ ያልቀደዱ መሃይምናን አይደሉም። በተሰለፉበትና በቀየሱት የፖለቲካ መስመር ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚደርሱ ጠንቅቀው የሚያውቁና ይህንንም ዕምነታቸውን ከመጀመሪያዋ የመንግሥትነት ቀናቸው ዠምሮ በተግባር ያስመሰከሩት እንጂ።

ህወሃት/ኢህአዴግ በመንግሥትነት ስንቀመጥ እንፈጥመዋለን ያሉትን ፈጥመዋል። የፈጠሙትና እየፈጠሙት ያለው ካለማወቅ ተሳስተው ሳይሆን አውቀውና አምነውበት ነበር፤ ነውም።

2. 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ለረዥም ዓመታት በኢህአዴግ ላይ የያዙትና ሲያራምዱት የኖሩት የፖለቲካ መርህ/መመሪያ ደግሞ *"ድርጅቱ ሲሳሳትም አውቆ ለክፋት አይደለም፤ ካለማወቅ ሊሆን ይችላል"* በመሆኑም *"ሂሳዊ ድጋፍ"* እየሰጡ ከስህተታቸው በማረምና ለወደፊቱ ስህተት እንዳይሰሩ በመምከር ማስተካከል ይቻላል - የሚል ነበር። ለመሆኑ ህወሃታውያኑ የነፃነት ጎህ ሲቀድን ጠሀፊ የፖለቲካ ስሌት ጠንቅቀው የሚያውቁትን ወይም የተረዱዋቸውን ያህል እሳቸው እነሱን ምን ያህል ያውቁዋቸው ነበር? ብለን ልንጠይቅ እንገደዳለን - መልስ ባይኖረንም ቅሉ።

ደ/ር ብርሃኑ በግልም እያገኘሁት ስህተታቸውን እነግረው ነበር ያሉን አንዱ ቀንደኛ ባንዳ በረከት ስምዖን የቢቢሲው ጋዜጠኛ ካቀረበለት ጥያቄዎች ውስጥ 'አሰብ የማን ናት?' የሚከተለውን በመጥሀፉ አካትቷል፤ (ባንዳው በረከት ባለማወቅ በስህተት የተናገረው ይሆን?)

*ሚስተር ሮቢን ኋይት (የቢቢሲው ጋዜጠኛ) አሰብን አስመልክቶ አቶ በረከትን ለጠየቋቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው መልሰውለታል፤*

*"እኛ የአሰብን ወደብ አንፈልገውም። መንግሥታችን አቋሙን በግልፅ ነው ያስቀመጠው፤ በአልጀርስ ስምምነቱ ላይ የትኞቹ አካባቢዎች የእኛ እንደሚሆኑ በትክክል አስቀምጠናል። በዚህ ወቅት የአሰብ ወደብ ከጥያቄያችን ውስጥ አልተካተተም። ጥቂት ኢትዮጵያውያን የ አሰብን ወደብ የኢትዮጵያ ግዛት አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝቦች አሰብን አይጠይቁም። ምክንያቱም የአሰብ ወደብ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ነች ይላሉ። ጅቡቲም ቢሆን እንደዚሁ ተመሳሳይ ጠቀሜታ አለው። የቅኝ ግዛት ውሎች አሰብን የኢትዮጵያ አካል አድርገው ባለማካለላቸው የይገባኛል ጥያቄ ለማንሳት የምንሄድበት ምክንያት አይኖርም።"* (አፅንዖት የቃኚው)

ይህ እንግዲህ በኢትዮጵያ የኤርትራ ጉዳይ ፈፃሚ የሆነው የባንዳው የኢህአዴግ አመራር የበረከት ብቻ አቋም ሳይሆን የባንዳዎቹ ሁሉ፤ የመለስ ዜናዊ፤ የስዩም መስፍን፤ የስብሃት ነጋ ወዘተ ወዘተ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩበት ቀንና ሰአት ዠምሮ የነበረ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ሲሆን እንዲህ ያሉትን ወይራ ባንዳዎች እንደምን አድርጎ በነበረ ስሌት ይሆን 'ድርጅቱ ሲሳሳትም አውቆ ለክፋት አይደለም ካለማወቅ ሊሆን ይችላል' የሚል አዎንታዊ አመለካከት የነፃነት ጎህ ሲቀድ ጠሀፊ ቢያንስ እስከ 1997 ዓ/ም ወይም ቅንጅትን የፈጠሩት ድርጅቶች እስከተፈጠሩበት ድረስ ሊኖራቸው የቻለው? ብለን እንድንብሰለሰል ያስገድደናል 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ'ን ስናነብ።

ለመለስ ዜናዊ፤ በረከት ስምዖንና ሌሎች ባንዳዎች ኢትዮጵያውያን የምንስተላልፍላቸው መልዕክት ግን አለን፤ እነሆ መልዕክታችን ከ'አሰብ የማን ናት?' የምናስተላልፈው፤

*"ኢትዮጵያ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አሰብ ካልተመለሰላት ችግሩ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው እየተላለፈ በቦሊቪያ እንዳለው ቁስሉ እያመረቀዘ ይሄዳል እንጂ ኢትዮጵያውያን መቼም የሚተዉት ጉዳይ አይሆንም። ቦሊቪያ በ1883 ዓ/ም ከቺሊ ጋር ባደረገችው ጦርነት የባህር ጠረፍ ግዛትዋ በቺሊ ተወሰደባት። ቦሊቪያ የባህር በር ሲወሰድባት ነፍሷ ከዚያው ጋር ሄደ እያሉ ቦሊቪያውያን ይገልፁታል። ቦሊቪያ የባህር*

*ጠረፍ ግዛትዋ ከተወሰደባት ጀምሮ ወደ አምስት ሺህ የሚጠጋው የባህር ሃይሏ አንድ ቀን የባህር ጠረፍ ግዛታችን እናስመልሳለን በሚል ተስፋ እስከ ዛሬ በቲቲካ ሃይቅ የባህር ላይ ጦርነት ልምምድ ያደርጋሉ። እንደ ቢቢሲ ዘገባ የቦሊቪያ ዜጋ ሁሉ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገው ቺሊ የባህር ጠረፋችንን ሰረቀችን ሲባል እየሰማ ሲሆን እርሱም በተራው ለልጆቹ ይህንኑ እየነገረ ያሳድጋል። ማንኛውም ቦሊቪያዊ አገርህ ወደብ አልባ ሆነች ሲሉት በምንም አይነት የማይቀበለው ሲሆን ህዝቡም በየዓመቱ 'የባህር በር የተወሰደበትን' ቀን ዘክሮ ይውላል።…*

*"የአሰብ ችግርም ለሁለቱም፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ በቶሎ ይፈታል አልያም እንደ ቦሊቪያው ችግር ተንጠልጥሎ ይቆያል እንጂ መቼም ቢሆን ኢትዮጵያውያን የሚተዉት ጉዳይ አይደለም። በመሃሉ ግን ለሁለት ወንድማማችና እህትማማች ህዝብ ለእልቂት መንስኤ ሊሆን መቻሉ ግን አሳዛኝ ነው።*

*"…በአገራችን አባባል 'እርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ' እንደሚሆን አንጠራጠርም።"* (አፅንዖት የቃኚው)

እንቀፅል።

ከ'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የሚከተለውን ነቁጥ ደግሞ ያስተውሏል፣

*"ኢህአዴግ ሀገሪቱ ወደፊት እንድትሄድ ሊጫወት ይችል የነበረውን ሚና እየሚጠጠ አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ነው የሚለው ስሜት ላይ የደረስኩት ከ1993 ዓ/ም የተማሪዎች ግጭት ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል።"* ገጥ 11 (አፅንዖት የኔ)

ልብ በሉ፣ በተለይ ከ1990ዓ/ም ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ዠምሮ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ነበረች። የአሰብ ጥያቄ እንደ እሳተ ገሞራ ፈንድቶ ድፍን ጠቢያን ያነቃነቀበት ዘመን ነበር። የኢትዮጵያ ምሁራን በሀገር ውስጥና ከውጪም አሰብን የ ኢትዮጵያ አካል ለማድረግ ለህወሃት መሪዎች ህጋዊና ታሪካዊ መረጃዎችን በማጉረፍ ላይ ነበሩ። የሀገር ውስጥ ነፃ ሚዲያዎች ያለማቋረጥ ምሁራኖቻችን ያሰባሰቧቸውን የታሪክና የህግ መረጃዎች ለህዝብ በማቅረብ በፍልሚያው ትንቅንቅ ውስጥ ነበሩ። የህወሃት መሪዎች ባንዳነት አደባባይ ሲወጣም በርካታ ምሁራን የታሪክ ሽፍጠኝነታቸውን በመተንተን ግልፅ ደብዳቤዎች ለባንዳዎቹ መሪ መለስ ዜናዊ ሲፅፉ ይህንንም ነፃ ሚዲያዎች ህዝባችን እንዲያውቀው ያደርጉ ነበር። ታዲያ በጦርነቱና ከጦርነቱም በኋላ የነበረው ትንቅንቅና የህወሃት ባንዳነት በእንደምን ያለ ስሌት ቢታይ ነው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ከቶም አንድም መስመር ሳይጥፍበት '…ከ1993 ዓ/ም የተማሪዎች ግጭት ጀምሮ ነው ኢህአዴግ አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ነው…' ብሎ የሚነግረን? ብለን እንጠይቅ ዘንዳ ራሱ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ያስገድደናል።

እነሆ በ1993 ዓ/ም ህወሃት ለአስር ዓመታት በሥልጣን ላይ ቆይቷል። በአስሩ ዓመታት እድሜው ህወሃት/ኢህአዴግ በሀገራችንና በህዝባችን ላይ ያደረሰው ሰቆቃና በደል፣ ያፈናቀለውና የገደለው አርሶ አደር ብዛት፣ ሀገራችንን በማፍረስ የተጫወተው ማጣፊያው የሚያስቸግር ጥፋት በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ፍፃሜ ያካሄደው ወደር አልባ ክህደት ወዘተ ሁሉ ከ1993 ዓ/ም የተማሪዎች ግጭት በስተቀር የነፃነት ጎህ ሲቀድ ጠሀፊ አልታያቸውም ነበር ማለት ነው? እንላለን እኛ ታሪኩ የቀረበልን በ'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የታሪክ ዘገባ ላይ ስሜታችን እየታመሰ።

ያም ሆነ ይህ ግን ኢህአዴግ/ህወሃት በአስሩ የአገዛዝ ዓመታት ውስጥ (ከ1983 ዓ/ም-1993ዓ/ም) ከፖለቲከኛ ምሁራኑ የሚሰጠውን "ሂሳዊ ድግፍ' በአንድ ጆሮው እየሰማ በሌላው እያፈሰሰው የአገዛዝ መዋቅሩን በሚገባ ሲዘረጋና ሲያጠናክር ኖሯል።

እናቅና ወደ ቀጣዩ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ነቁጥ፤

*"እኔ በብዙ ታዛቢዎች ዘንድ የኢህአዴግን ባህሪ በቅጡ የማላውቅ ተደርጌም ተወስጃለሁ። ለዚህም ዋናው ምክንያት ከኢህአዴግ ባህሪ በመነሳትም ባይሆን ኢህአዴግና መሪዎቹ ዘላቂ ጥቅማቸውን ያውቃሉ ከሚል ስሌት ቀስ በቀስ እንዳይደነብሩ በስልት ከተያዙ የዲሞክራሲ ሽግግሩን በሠላማዊ መንገድ ለማድረግ ይተባበራሉ፤ የዓለምን ታሪክ ሂደት ይገነዘባሉ፤ እያደር ከዲሞክራሲና ከነፃ ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይረዳሉ የሚል እምነት ስለነበረኝ ነው። አሁንም "የአዎንታዊ በሽታ በሉት እንጂ ሙሉ ለሙሉ ተስፋዬን አልቆረጥኩም።"* ገጥ 113 (አፅንዖት የኔ)

አንባቢ ሆይ! 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ይህንን እጅግ አስገራሚ፤ አስደንጋጭና አሳዛኝ አባባል ያሰፈሩት ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝብ ድምፅ ማጅራት መትቶ ሌሎች የፖለቲካ መሪዎችን ጨምሮ እሳቸውም የኢህአዴግ ሰለባ ከሆኑበት ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ሆነው ነው። በ1998 ዓ/ም በግፍ ከታሰሩበት እስር ቤት (ከአስራ አምስት ዓመታት የኢህአዴግ ኢፍትሃዊ አገዛዝ በኂላ) እንኳን በኢህአዴግ ላይ 'አንጀታቸው ሊቆርጥ' አለመቻሉ አስገራሚ አስደንጋጭና አሳዛኝ የሆነው በሶስት ምክንያቶች ይሆናል።

አንደኛው፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሊከሰት ያልቻለና እሳቸው ብቻ የሚያውቁት የ ኢህአዴግ/ህወሃት መሪዎች ሊለወጥ የሚችል ባህሪ ከቶ ምን ነበር? የሚለው ይሆናል።

ሁለተኛውና ከአስገራሚነቱ አስደንጋጭነቱ የሚያመዝነው *"የአዎንታዊ በሽታ"* በሉት ያሉን በኢህአዴግ/ህወሃት መሪዎች ላይ ያላቸው እምነት የሚያስከትለውን ፖለቲካዊ አንደምታ አለማየታቸው ይሆናል።

እርሳቸውንና ከእርሳቸው ጋር ወህኒ የገቡትን መሪዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ከዘረኛውና ሀገር ሻጩ የኢህአዴግ/ህወሃት መሪዎች ይገላግሉኛል በማለት ፀሀይና ቁር፤ ረሃብና ጥም ሳይበግሩት መርጧቸው ሲያበቃ እሳቸው ግን እስር ቤት ሆነው **"በኢህአዴግ ላይ አሁንም ተስፋ አልቆረጥኩም"** ብለው በመጥሀፋቸው ሲነግሩት የህዝባችንን የትግል ቅስም እንክት ማድረጋቸው ብቻም ሳይሆን በታሰሩትና ወደፊትም በሚነሱት የህዝብ መሪዎች ላይ አመኔታ እንዲያጣ ማድረጋቸው መሆኑን አለማየታቸው ወይም ቦታ አለመስጠታቸው እጅግ አሳዛኛና አስገራሚም ነው።

በሶስተኛም ደረጃ እንዲሁ አሳዛኝ የሚሆነው ደግሞ ሌላው ቢቀር እንኳን ቢያንስ በምርጫ '97 እሳቸውን (ዶ/ር ብርሃኑን) እና ሌሎቹን መሪዎቹን በአደባባይ ከኢህአዴግ/ ህወሃት በፊት ቅድሚያ ሰጥቶ በመምረጡ ምክንያት በግፈኛው የአጋዚ ጦር ለተጨፈጨፉት ሰማዕታት ክብርና ለቤተዘመዶቻቸውም ስሜት ሲባል ይህንን በኢህአዴግ ላይ ተስፋ ያለመቁረጥ *"አዎንታዊ በሽታ"* በዚህ መጥሀፍ ላይ በዚህ መልክ ከመግለፅ አለመታቀባቸው ነው።

ከዚሁ ጭብጥ ሳንወጣ የሚከተለውን ነቁጥ ደግሞ ልብ ይሏል፤

*"አቶ መለስ ለ14 ዓመታት ባልተገደበ ሥልጣን ላይ ቆይቷል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በጣም ጥሩ የሚባል ተቀባይነት ከውጪው ዓለም ዘንድ አግኝቷል። በፈለገ ጊዜ ታላቅ የፖለቲካ*

*ሰው ተብሎ እስከ ዕለተ ሞቱ ተከብሮ መኖር የሚችል እንዲሆን ታሪክ እድል ሰጥቶታል። በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ዲሞክራሲና ነፃ ማህበረሰብ የፈጠረ ተብሎ በታሪክ ስሙ ለዘለዓለም ገንኖ ሊወራለት እንደሚችል ያውቃል። ታዲያ ይህ ሰው … በግልፅ በማጭበርበር ወይም ዐይን ያወጣ ጉልበትን በመጠቀም ይህንን ቆንጆ ታሪክ ዝም ብሎ ይጥለዋል ብዬ ለማመን ከብዶኛል። በተለይ ይህንን ታሪክ አበላሽቶ የሚገኘው ጥቅም ምን ሊሆን ይችላል ብዬ ሳስብ በፍፁም አጥጋቢ መልስ ላገኝለት አልቻልኩም።"* ገጥ 113 — 114 (አፅንዖት የኔ)

አንባቢ ሆይ! በበኩሌ በሀገሩ ጉዳይ እንደሚብከነከን አንድ ኢትዮጵያዊ መልስ ያላገኘሁለት ጥያቄ ቢኖር፤ ለአስራ አራት ዓመታት (እስከ 1997 ዓ/ም) ዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያለፈበትን ታሪክ በዳሰሱበት መጥሀፍ ውስጥ እንዴት እንዲህ ያለ ቅስምን የሚሰበር፤ ልብን የሚያደማ ታሪክ ያቀርቡልናል? የሚለው ነው።

እንደ ባቢሎን ግንብ ሠራተኞች መግባባት የማንችል ካልሆነ በተቀር አቶ መለስም ሆኑ የኢህአዴግ/ህወሃት መሪዎች የቆሙለትንና የሚያምኑበትን ታሪክ ሠርተዋል። እነሱ ሌላ ታሪክ አይፈልጉም።

ለነሱ ታሪክ ማለት ኢትዮጵያዊነትን አጥፍቶ፤ ኢትዮጵያንም አሽመድምዶና ሽባ አድርጎ (ለምሳሌ ወደብ ማሳጣቱ) ጎጠኝነትን የሚያራምድና ጎጠኝነትን የሚያስፋፋ መንግሥት መፍጠር ነበር፤ ፈጥረዋል።

ለነሱ ታሪክ ማለት በዲሞክራሲ ስም የህዝብን መብት መርገጥ፤ ህዝብ በገዛ ሀገሩ ባይተዋርነት እንዲሰማውና ከአንድ ክፍለ ሀገር ወደ ሌላው ሄዶ ነግዶም ሆነ አርሶ ወይም ኑሮ መስርቶ የመኖር የዜግነት መብቱን በ"ክልል" አጥር ማሰር ነበር፤ አድርገዋል። ሌላም…ሌላም።

'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ *"አቶ መለስ ይህንን ቆንጆ ታሪክ ዝም ብሎ ይጥለዋል ብዬ ለማመን ከብዶኛል"* ይሉናል - የህዝብን ድምፅ በጠመንጃ አፈሙዝ ያገተውንና በግፍ ያሰራቸውን አምባገነን ዘረኛና ባንዳ መሪ።

ይባስ ብለው ደግሞ *"አቶ መለስ ይህንን ለምን እንደሚያደርግ ባስብም አጥጋቢ መልስ ላገኝለት አልቻልኩም"* በማለት የመርዶ ያህል አርድተውናል። የእናንተን ባላውቅም በበኩሌ ግን እስካሁን ካቀረብኩት የአምባገነኑና ዘረኛው አቶ መለስ ፓርቲ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥፋት ሌላ ለእሳቸው (ለዶ/ር ብርሃኑ) በዚያን ወቅት አጥጋቢ ሊሆን የሚችል መልስ ምን ይሆን እንደነበር እንቆቅልሽ ሆኖብኛል።

'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ "ይህንን ቆንጆ ታሪክ' የሚሉት ሥልጣኑን የማስረከቡ ጉዳይ ከሆነ ያም ቢሆን ወቅቱ በፈጠረው አጋጣሚ አማራጭ ሃይል ያገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃት/ኢህአዴግ በቃን አንገፈገፈን፤ ሀገር አሳጣን፤ በዘር ከፋፈለን፤ ብሎ ድምፀ ተዐቅቦ አድርጎበት በመሆኑ ነበር እንጂ በመለስ ዜናዊ መልካም ፈቃድ ሆኖ አልነበረም። አቶ መለስና ጋሻጃግሬዎቻቸውም ህዝቡ በጠመንጃቸው ፍርሃት ተጀቡኖ የሚገኝ ስለመሰላቸውና ከዳር እዳር ተነቃንቆ በመውጣት አይናችሁ ላፈር ይለናል ብለው ስላልገመቱም ጭምር ነበር ምርጫ ማለታቸው። ውጤቱም ከህወሃት ተፈጥሮ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ያጠለቁትን ካባ ለማውለቅ ጊዜም አልወሰደባቸው። 'ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም' ይላሉ እኒያ ጥንታውያን። ህወሃት በተፈጥሮው ቆንጆ ታሪክ ኖሮትም አያውቅምና ሥልጣኑን ቢለቅም ኖሮ በወንጀለኝነት የሚጠየቅባቸው የሀገር ክህደት፤ የዘር ማጥፋትና የመሳሰሉት ወንጀሎች ብዙ ነበሩ።

ለመሆኑ ኢ.ህአዴግ በታሪክ ታሪኩ እንደምን ይዘገባል? እንጥቀስ ከ'አሰብ የማን ናት?'

*'ኢ.ትዮጵ.ያ የባህር በርዋ አሰብ እስካልተመለሰላት ድረስ ኢ.ህአዴግ በየትኛውም በጎም ይሁን መጥፎ ሥራዎቹ የባህር በር ማዘጋቱ ከሁሉም በላይ ጎልቶ ይወጣል። አሰብ ለ ኢ.ትዮጵ.ያ እስካልተመለሰ ድረስ ዘመናት አልፈው ዘመናት ሲተኩ በጊዜው ኢ.ህአዴግ ማን ነበር ሲባል መልሱ መንገዶችን፣ ትምህርት ቤቶችን ወይም ሐኪም ቤቶችን ያነፀው አይሆንም። መልሱ የኢ.ትዮጵ.ያን የባህር በር ያዘጋው መንግሥት ነው የሚሆነው።"* ይላል ማጣቀሻችን 'አሰብ የምን ናት?' (አፅንዖት የቃኚው)

በዚ.ያን የጦርነት ማግሥት ህወሃት አሰብን አልጀርስ ላይ ለኢ.ሳያስ አፈወርቂ በ አደራዳሪዎች ፊት ዳግም በፊርማ ለማስረከብ ለኤርትራ ጥብቅና የቆሙ ተደራዳሪዎችን በዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር ቀጥሮ ሽብ እረብ በሚልበት ወቅት አያሌ  የታሪክና የህግ ኢ.ትዮጵ.ያውያን ምሁራን መረጃዎችን በማሰባሰብና ለመንግሥት በማቅረብ መንግሥት አሰብን ሊ.ያስመልስበት የሚችልበትን ታሪካዊ፣ ህጋዊና ዲፕሎማሲ.ያዊ ዘርፎች ሁሉ አቅርበውለት ነበር። በወቅቱ የቀረቡለትን መረጃዎች ሁሉ መጥቀስ የማይቻል በመሆኑ ለዚ.ህ ቅኝት ማጣቀሻ እየተጠቀምኩበት ካለው 'አሰብ የማን ናት?' ውስጥ ዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማርያም **ከ1997 ምርጫ አምስት ዓመት በፊት** ነሀሴ 11 ቀን 1992 ዓ/ም ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከላኩት ሠፊ ግልፅ ደብዳቤ ላይ የሚከተለውን ነቅሻለሁ ወይም ቀንጭቤ.ያለሁ።

*ግልፅ ደብዳቤ*

*ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ*
*የኢ.ትዮጵ.ያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲ.ያዊ ሪፑብሊክ*
*ጠቅላይ ሚኒስትር*
*አዲስ አበባ*

*ክቡር ሆይ*

*...ሚሊዮን ጦር ቢ.ያሰልፉ ሀውልት ቢ.ያንፁ እንደ መብረቅ ቢፈሩ ሁሉም ጊዜውን ጠብቆ አላፊ ነው። ከአፈር ገፊው ገበሬ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚ.ህ ዓለም ሳያልፍ በምን እታወሳለሁ ብሎ ራሱን መጠየቁ አይቀርም። እርስዎም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትርነትዎ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አመራሬ መንግስቴ በምን አይነት ይታወሳል፣ በምንስ ይመሰገናል፣ በምንስ ይወቀሳል ብለው መጠየቅ ያለ ነው። ታሪክ አድልዖ አያውቅምና ሁሉም እንደስራው ሞገስም ሆነ ወቀሳ መለገሱ አይቀርም።*

*...ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የእርሶም መንግሥት ከሚታወቅበትና ከሚገመገምበት ከዋነኛዎቹ ሚዛኖች አንዱ "አሰብን ለሌላ አስረክቦ ኢ.ትዮጵ.ያን ለዘንተ አለም ወደብ አልባ አድርጎ በየብስ የከረቸመ" ወይንም ደግሞ "በህግ በታሪክ የኢ.ትዮጵ.ያ አንጡራ ሀብት የሆነችዋን አሰብን በረቀቀ ዲፕሎማሲ.ያዊ ትግል አስገኝቶ ለኢ.ትዮጵ.ያ ባህር በር ዋርድ.ያነት የቆመ" መንግሥት ተብሎ ነው። ለማንም ቢሆን ሚዛን የሚደፋው ምርጫ ሁለተኛው ለመሆኑ አያጠራጥርም።...*

*...የኢ.ትዮጵ.ያ ዲፕሎማሲ.ያዊ ትግል ሰልሎ ኢ.ህአዴግ ወኔ ከድቶት ይህንን ሀልቀመሳፍርት መስዋዕትነት ለከፈለው፣ ጦር መጣ ባሉት ጊዜ ለደቂቃ ሳያመነታ ጥሪውን አክብሮ ቀፎው እንደተነካ ንብ ተምሞ ለወጣው ለደጉ የኢ.ትዮጵ.ያ ህዝብ እጅግ ቢ.ያንስ አንድ ሊ.ያደርጉለት*

*የሚችሉት ነገር አለ። መንግሥትዎም አሰብን የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት ሊያደርግ ካልፈለገ ወይንም ካልቻለ ቢያንስ ቢያንስ ድንበር በሚከለልበት ወቅት የአሰብን ጉዳይ ከድርድሩ መዝዞ አውጥቶ "አልስማማም" ከማለት የሚያግደው ነገር ያለ አይመስለኝም። ህጋዊነት እየተጠበቀ ከዚያም አልፎ መሄድ ይቻላል።…መንግሥትዎ የአሰብን ጉዳይ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እስከፈታ ድረስ ድንበር አልካለልም እንኳን ቢል የዓለም ዐቀፍ ህግን ጣሰ ማለት አይቻልም።…ከአፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒልክና አፄ ሃይለሥላሴ የደከሙለት በመጨረሻም በአፄ ሃይለሥላሴ ዘመን እልባት ያገኘው የባህር በር ጉዳይ ዛሬ በችኮላ የዓለም ህብረተሰብ ዋስትናነት በተንተራሰ ውል ኢህአዴግ የአሰብ ጥያቄ ቢለቅ የመጪው ትውልዶች መብት ከእግራቸው ስር ሰረቀ ማለት ነው። **አሰብ ወደ ኤርትራ ሲካለል ነው የኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ የተዋደቁት የኢትዮጵያ ጀግኖች አፈሩ የሚከብዳቸው።…***

*ድንበር መካለሉ ለኤርትራውያን እንጂ ለእኛ ኢትዮጵያውያን እጅግም አስፈላጊያችን እንዳልሆነ የሚያጡት አይመስለኝም። ለክቡርነትዎ በትህትና ላሳስብ የምፈልገው ለ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የጦርነቱም ሆነ የድርድሩ አልፋና ኦሜጋ ድንበር መካለል አይደለም፣ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነትን ማረጋገጥ እንጂ። የኢትዮጵያ ህዝብ የባህር በር ባለቤትነት ሉአላዊነት ከማስከበሩ አሳንሶ አያየውም። እንደ መራሂ መንግስትነትዎ የ ኢትዮጵያን ሉአላዊነት ማስከበር ካለብዎት ሃላፊነት የአሰብ የባህር ወደብ ወደ ኢትዮጵያ የማጠቃለል ሃላፊነት ትልቁ ነው። ሆኖም ግን መንግሥትዎ ወይንም ድርጅትዎ በ አብዛኛዎቻችን ግምት የኢትዮጵያ መፃኢ እድል ወሳኝ የሆነው የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ አምኖበት ሊታገል ካልፈለገ 'ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል' አይነት ስለሆነ ፍርዱን ለታሪክ ከመተው ሌላ ለአሁኑ ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም።*

*ከማክበር ሰላምታ ጋር*
*ያዕቆብ ሃይለማርያም*

*(አፅንዖት የቃኚው ሰረዝ የመጥሁፉ)*

**እነሆ ለዚህና ይህንን ለመሳሰሉት የሌሎች በርካታ ኢትዮጵያውያን ምሁራን የዕንባና የደም ተማፅኖ ጥሪ የአቶ መለስ ዜናዊ ምላሽ ምን ነበር? ባንዳነት!!**

አንባቢ ሆይ! በምርጫ 97 ባንዳ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ባለመልቀቃቸው 'ታሪካቸውን አበላሹ' የሚል አንደምታ ያለው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' አገላለፅ - *ይህንን ቆንጆ ታሪክ (ሥልጣን መልቀቁን) ዝም ብሎ ይጥለዋል ብዬ ለማመን ከብዶኛል*- በማለት ከቃሊቲ እስር ቤት ሆነው ሲጥፉልን ለመሆኑ እስካሁን የዘረዘርነው በወቅቱ በህወሃት/ኢህአዴግ የተተገበሩ መዘዘ ብዙ የፖለቲካ ጥፋቶችን እንደምን መለስ ብለው ለመመርመራና ለማመዛዘን ግድ አልሰጥ አላቸው? የሚለው እንደ ሌሎቹ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሁሉ የእኛን ታሪክ ለእኛው ያቀረበልንን የነፃነት ጎህ ሲቀድ ስናነብ ከአእምሯችን እያፈተለከ የሚወጣ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው።

'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ለኢህአዴግና ለመሪዎቹ የነበራቸው አዎንታዊ የተማከለ ፖለቲካዊ አመለካከት እስከ *መጥሁፉ ገፆች መገባደጃ* (614 *ገፆች አሉት*) የዘለቀ ሲሆን ኢህአዴግ የህዝብን ድምፅ ሰይፎ ወደር አልባ ግፍ ከፈፀመ ከስድስት ወር በኍላ እንኳን የሚከተለውን አስደማሚ አገላለፅ አስቀምጠውልናል።

*"የኢህአዴግ ስሌት እኔ የምለውን ያህል ስህተት ከሆነ ከምንም በላይ ስለ ኢህአዴግ የሚጭረው ጥያቄ አለ። ይኸውም እንዴት ኢህአዴግን የሚያክል ብዙ ዘመን ያስቆጠረ፣*

*በርካታ በፖለቲካ 'የበቃን ነን' የሚሉ አባሎች ያሉት፣ የመንግሥት ሥልጣን በመያዙና ብዙ ንብረት ስላለው በገንዘብና በጥቅም የገዛቸው አማካሪዎች ያሉት ድርጅት እንዴት እንዲህ አይነት ከባድ ስህተት ሊሰራ ይችላል? የሚለው ነው። እውነት ለመናገር ከታሰርኩ ጊዜ ጀምሮ ይህን ጥያቄ ደግሜ ደጋግሜ ለማየት ሞክሬያለሁ።...ከአንዳንድ ሩቅ ከማያስኬዱ የሴራ ንድፈ ሀሳቦች በስተቀር አመርቂ የምለው መልስ አላገኘሁለትም።"* ገጥ 583 (*አፅንዖት የኔ*)

ለዚህ እጅግ አስደማሚና ደግሞም እጅግ አስደንጋጭ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ግምገማ ምክንያቱ እንደ ኢህአዴግ ያለ ድርጅትንና ምላጭ መሪዎችን በ'ሂሳዊ ድጋፍ' ወይም 'ያለምንም ፍርሃቻ' ስህተታቸውን በመንገር ተፈጥሯቸውን እንዲቀይሩና ለኢትዮጵያዊነትና ለኢትዮጵያ ጥቅም ቆመው በትክክለኛው የዲሞክራሲ ሀዲድ ላይ ፖለቲካውን እንዲሾፍሩ ማድረግ ይቻላል በሚል ለአስራ አራት ዓመታት በዘለቀው 'የነጻነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ፖለቲካዊ ዕምነት ነበር ብለን ብናምን እንኳን እንዴት በእስር ላይ እያሉ ያለፉትን ዘመናት የኢህአዴግ አመራርና እኩይ ተግባራት መርምረው መመልከት ቢያቅታቸው ነበር አስቀድመን እንዳነበብነው *"...ከታሰርኩ ጊዜ ጀምሮ...መልስ አላገኘሁለትም"* እስከ ማለት ያደረሳቸው? ብለን ራሳችንን እስኪያመን ድረስ መልስ ለማግኘት እንብሰለሰላለን።

*"ኢህአዴግ ቢሳሳትም አውቆ ለክፋት አይደለም ካለማወቅ ሊሆን ይችላል..."* የሚለው ፖለቲካዊ አቋም እጅግ አደገኛና የፖለቲካን መርህ /ፕሪንሲፕል በአፍጢሙ የደፋ (ከህወሃት የአመታት እኩይ ምግባር አኳያ) አመለካከት የነበረ ሆኖ እናገኘዋለን 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ'ን ስናነብ።

የኢህአዴግ መሪዎች ተፈጥሮ በ'ሂሳዊ ድጋፍ' ሊቀየር ይችላል የሚለው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ፖለቲካዊ አቋም 'ከእባብ እንቁላል ርግብ ይወለዳል' እንደ ማለት የነበረ ለመሆኑ ነባራዊው የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተግባር ያሳየ ሀቅ ነው።

<u>ዩቶፒያ - ኢትዮጵያ</u>

*"እስር ቤት እንደ ገባን ሌሊት ላይ የተደበደበ ሰው ጩኸት እንሰማ ነበር። በመጀመሪያ ማመን ነበር ያቃተን። ሠቆቃ (ቶርቸር) በኢትዮጵያ የለም ብለን እናምን ስለነበር ስንሰማው ግራ ተጋባን። አነ ስዬ ከመጡ በኋላ እንደዚሁ አንድ ሌሊት ይህንን የሰው የስቃይ ጩኸት ስንሰማ አድረን ጠዋት ስዬን ሠማኸው ወይ የማታውን ስለው እሱም መስማቱንና ማመን እንዳቃተው፣ እንዲህ አይነት ነገር እንዳለ እንደማያውቅ ነገረኝ። 'ይህ ነው እንግዲህ የታገላችሁለት' ብዬ እንደ ቀልድ ጣል አደረግሁ።"* ገጥ 199 የግርጌ ማስታወሻ (*አፅንዖት የኔ*)

አቶ ስዬ አብረሃና ጓዶቻቸው የመሩት ድርጅት ህወሃት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበትና እሳቸው (አቶ ስዬ) እስከታሰሩበት ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰቆቃ (ቶርቸር) ነበር ብለው እንደማያምኑ ቢነግሩን አይደንቀንም። የኮረኮሩን ያህልም አያስቀንም።

ይሁንና ይህንን አይናችንን ማመን እስኪያቅተን ድረስ መላልሰን እንድናነበው የሚያስገድደንን አስገራሚና ባይተዋር ዕምነት የነገሩን የኢትዮጵያን ህዝብ ብሶትና እንግልት፣ ዋይታና ሠቆቃ ያውቃሉ የምንላቸው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ ናቸው።

እንኳንና መነሻውና መድረሻው የዘር ፖለቲካ በሆነው ኢህአዴግ/ህወሃትን በመሰለ አምባገነን ድርጅት በምትገዛዋ ኢትዮጵያ ቀርቶ የዲሞክራሲ ቁንጮ ናቸው በሚባሉት የ

አንደኛው ዓለም ሀገሮች ውስጥም ሠቆቃ (ቶርቸር) — (በተለያየ ገፅታውና መልኩ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች) - የለም ብሎ ለመናገርም ሆነ ለማመን በእጅጉ አስቸጋሪ ነው።

'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ጠሀፊ በግፍ እስከታሰሩበት ዘመን ድረስ ኢህአዴግ በየእስር ቤቶችም ውስጥ ሆነ በክልል አጥር ባጠራቸው የሀገሪቱ ግዛቶች በሙሉ ምናልባትም ከዚህ ቀደም በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ሥነ ልቡናዊ (ሳይኮሎጂካል) እና አካላዊ (ፊዚካል) ሠቆቃ (ቶርቸር) በህዝባችን ላይ ሲፈፅም ለመኖሩ የዚህ ቅኝት አቅራቢ ማስረጃዎችን መደርደር አይጠበቅበትም፣ ህልቆ መሳፍር ናቸውና። ይሁንና ከላይ በነቀስኩት 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' አገላለፅ ዕውነታነት አንጣር አንባቢ የራሱን ግንዛቤ መውሰድ ይቻለዋል።

እናምራ ወደሚከተለው ነቁጥ፣

*"…በሁለተኛው ቀን አንድ ጠና ያለ እስረኛ ፀሀይ በምንሞቅበት ሠዐት ጮክ ብሎ በጥቅሉ ያለን 'እናንተ እስካሁን ሠብዐዊ መብት ትላላችሁ። ገና አልገባችሁም። ወይም አውቃችሁ አይናችሁን ጨፍናችኋል። እዚህ አገር ያለው የዘር አገዛዝ ነው። ግልፅ የሆነ የዘር ጭቆና ነው። ይህ መንግሥት እስካለ ድረስ ስለ ዜጎች እኩልነትና ሠብዐዊ መብት ማውራት ውሸት ነው' ሲል በማሾፍ በእኛ ላይ ተናገረ።"* ገጥ 22 (አፅንዖት የኔ)

እነሆ በአንዲት ሀገር ውስጥ በሁለት ዓለማት የሚኖሩ ዜጎች ይኗል ይህ ነው።

በአንደኛው ዓለም - በኢትዮጵያ ሠቆቃ የለም፣ ኢህአዴግ ወደ ዲሞክራሲ ቢዘገይም ሊያመራ ይችላል፣ ስህተቱም ካለማወቅ በስህተት የመነጨ በመሆኑ በ'ሂሳዊ ድጋፍ' እና በምክር ይስተካከላል ወዘተርፈ በሚለው ጎራ በዩቶፒያ ኢትዮጵያ (ምናብ ውስጥ ባለች ኢትዮጵያ) የኖሩ የፖለቲካ ልሂቃን ሲገኙ፣

በሁለተኛው ዓለም ደግሞ - በነባራዊቷ ኢትዮጵያ፣ ኢህአዴግ/ህወሃት ሥልጣን ከጨበጠበት 1983 ዓ/ም ዠምሮ አሰቃቂውን የዘር መድልዖ ፅዋ (በአርሲ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ወዘተ) ሲጋቱ፣ የጥይት ሰለባ ሲሆኑ፣ ያለ ፍትህ በእስር ሲማቅቁ፣ ለስደት ሲዳረጉ፣ ወልደው ከከበዱበት አካባቢ በመጤነት ተፈናቅለው ለአካላዊና ህሊናዊ ሰቆቃ (ቶርቸር) ሲዳረጉ ወዘተርፈ፣ ደግሞም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ በባዶ ሜዳ ያለ ውጤት ሲቀር፣ በአልጀርሱ ስምምነት ለኤርትራ በሚሟገቱ የኢህአዴግ ቅጥረኞች አሰብን የማስመለሱ አጋጣሚ እንዲጨናገፍ ሲደረግ፣ ወዘተርፈ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ አያሌ ዜጎች ይገኛሉ።

በነባራዊቷ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች (ለምሳሌ ሽማግሌዎቹና ተደብዳቢዎቹ እስረኞች) እና በዩቶፒያ ኢትዮጵያ (በምናብ ውስጥ ብቻ በምትገኘው ኢትዮጵያ) ነዋሪዎች መካከል ሀገራችን የነበረችበትን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እውነታ ቁልጭ አድርጎ በማየትና ወይም በመገንዘብ አንፃር በወቅቱ (ከ1997 ዓ/ም በፊት?) የነበረውን ከቶም የማይጣጣም ጉልህ ልዩነት አስቀድሞ ከተነቀሰው 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ማስረጃ በገሀድ መመልከት ይቻላል።

ቀድሞ ባነሳነው ነጥብ አኳያ በነፃነት ጎህ ሲቀድ ጠሀፊ ላይ የምናነሳው ጥያቄ ይኖረናል - የሚከተለው፣

ለመሆኑ የነፃነት ጎህ ሲቀድ ጠሀፊ ከ1997 ዓ/ም በፊት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የነበራቸው ቀጥተኛ ተሳትፎ ወይም ግንዛቤ ወይም በዘመኑ የታሪክ የህግና የኢኮኖሚ ምሁራን በሀገሪቱ የፖለቲካ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የህግ ጥያቄዎች አንፃር

*የህወሃት/አህአዴግን ኢፍትሃዊ ተገወባራት በማጋለጥና በማውገዝ ያቀርቧቸው በነበረ ፅሁፎች ወዘተ ላይ በህዝቡም መኻል ሲብላላ ለኖረው የተቃውሞ እንቅስቃሴም ሆነ የተቃዋሚ ድርጅቶች ምንነት፣ ዓላማና ግብ የሚያውቁት እስከምን ድረስ ነበር?*

*ለየህ ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ከራሱ ከመጥሀፉ እነሆ፣*

*"ወደ ፖለቲካው ሙሉ ለሙሉ እስከገባሁበት 1997 መጀመሪያ ድረስ እንደ ማንኛውም ዜጋ ጋዜጣ ከማንበብ ከሚገኘው መረጃ ውጪ ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረም።"* ገጥ 188 (*አፅንዖት የኔ*)

*ይህንን የነፃነት ጎህ ሲቀድ መረጃ ስናነብ ወደን ሳይሆን በራሱ በመጥሀፉ አቅርቦት የፊጢኝ ተገደን የሚከተለውን ጥያቄ ደግሞ እናቀርብ ዘንዳ እንገደዳለን። ለመሆኑ ወደ ፖለቲካው ዓለም በ1997 ቢገቡም ከዚያን በፊት በነበሩት ዘመናት የነበራቸው ፖለቲካዊ መረጃ/ዕውቀት ጋዜጣ በማንበብ ብቻም እንኳን ቢሆን ያነቡት የነበረው ጋዜጣ/ጋዜጦች የትኞቹን ነበር? ምክንያቱም በዚያን ዘመን የነፃው ሚዲያ ጋዜጦችና መፅሄቶች ለምሳሌ ኢትኦጵ ይዘግቡ የነበረው - ሌላው ቢቀር በጦርነቱ ወቅትና ከጦርነቱ በኋላም አሰብን ባንዳው ህወሃት እስካስረከበበት ድረስ ሰፊና ጥልቅ መረጃዎችን የያዙ ዘገባዎችንና ቃለ ምልልሶችን ነበርና - እኒህ ዘገባዎችን ይከታተሉ ከነበረ እንዴት በኢህአዴግ ላይ የነበራቸውን አመለካከትና እምነት ለመመርመር ሳይቻላቸው ቀረ?*

***<u>መደምደሚያ</u>***

*እነሆ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' መጥሀፍን ካነበብኩበት ወቅት ዠምሮ በህሊናዬ ሲመላለሱ የኖሩና ውስጤን ያብሰከሰኩኝን በሀገራች ሁነቶች ላይ የጠሀፊውን የተማከለ ፖለቲካዊ አመለካከቶች ከአንባቢያን ጋር ለመጋራት ተንፍሻለሁ።*

*የቅኝቴ መነሻም ሆነ መድረሻ 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ለእኛ ባቀረበልን የታሪክ ዘገባ ላይ እንደ መጥሀፍነቱ አንብቤ ያቀረብኩት ቅኝት ብቻ መሆኑን በድጋሚ ታዳሚያን ልብ ይሉልኝ ዘንዳም እጠይቃለሁ።*

*በዚህ ቅኝት የነቀስኳቸው አንኳር የምላቸው ነቁጦች ዛሬም ቢሆን አንገብጋቢ የሆኑና የሀገራችንን መፃኢ ዕድል የሚመለከቱም ናቸው ብዬ አምናለሁ፣ ለምሳሌ በአሰብ ጉዳይ ላይ ህብረብሄር የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ድርጅተነታቸውም ሆነ ወይም የፖለቲካ መሪዎችና ግለሰቦች እንደ ፖለቲከኛነታቸው የሚኖራቸው ግልፅና የማያሻማ አቋም ኢትዮጵያውያን የዘረኛና አምባገነኑን የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ለመጣል በሚያደርጉት ትንቅንቅ የተማከለ አሰባሳቢ ሀይል ነው የሚል ፅኑዕ ዕምነት አለኝና!*

*በሀገራችን በኢትዮጵያ ጭቆናን እና አምባገነንነትን፣ ዘረኝነትንና ፀረ ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግ በተደረገውና በሚደረገው መራር ትግል የትላንት የትግል ታሪካችንና የፖለቲካ ጉዟችን ለዛሬው ትንቅንቅ ጥርጊያውን በማቅናት መጪውንም ጉዞ በጠራ ራዕይና የትግል ቅያስ ለመምራት በትምህርትነቱ እንጂ መመርመርና መበራየት የሚኖርበት አላስፈላጊ ለሆነ እሰጥ እገባ መሆን አይኖርበትም። እንዲህ ያለው አካሄድም በእስከ ዛሬው ልምዳችን አንዲት ጋት እንኳን ሲያራምደን አላየንምና። የአሰብ ጥያቄም ኢህአዴግን ለመገርሰስ በሚደረገው ትንቅንቅ ውስጥ ድፍን ጦቢያን የሚያሰባስብ መሪ የፖለቲካ ጥያቄ ነውም ብዬ በፅኑ አምናለሁ። 'የነፃነት ጎህ ሲቀድ' ላይ ያቀረብኩትም ቅኝት መታየት የሚገባው ከዚህ አኳያ ይሆን ዘንዳ አስፈላጊ ነው። የቅኝቱ ፋይዳም፣* ***አንድም መጥሀፉ እንደ መጥሀፍነቱ***

**ካስተላለፈልን የታሪክ ጭብጥ አኳያ እንድንመረምረው አስፈላጊ በመሆኑ ሲሆን አብይ ኢላማውም ዛሬ ላይ ቆመን ትላንትን በመቃኘትና በመገምገም በነገይቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ አቅጣጫና መንገድ ላይ የጋራ ግንዛቤ ኖሮን በጋራ እንድንታገል የበኩሉን ግልጥ የውይይት አስተዋፅዖ ያደርጋል ከሚል ንፁህ ዕምነት አንጣር መሆኑን አንባቢያን አፅንዖት ይሰጡት ዘንዳ ከአክብሮት ጋር እጠይቃለሁ።**

**በያለንበት ቸር ይግጠመን!**

*መስፍን ማሞ ተሰማ*
*ታህሳስ* 2004 *ዓ/ም*
*ዲሴምበር* 2011

**ሲድኒ**
**አውስትራሊያ**

**ለአስተያየትዎ፤ የመልዕክት አድራሻዬ ይኸውልዎ፤** mmtessema@gmail.com

<u>*የመጣህፍት አድራሻ*</u>

1. ‘የነፃነት ጎህ ሲቀድ’ በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ - የመጥሀፉ አሳታሚ ድርጅት ስምም ሆነ ሌላ አድራሻ ከመጥሀፉ ማግኘት ስላልቻልኩ ማቅረብ አልቻልኩም።
2. “እሰብ የማን ናት?’ በዶ/ር ያዕቆብ ሃይለማርያም - ከመጥሀፉ ያገነሁትን የኢሜል አድራሻ እነሆ፤ yacobhm@gmail.com